https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የትራንስፖርት ሚኒስቴር

# Federal Democratic Republic of Ethiopia,

# Ministry of Transport

ሰኔ

June 2021

## የሙልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማስጠት እና ብቃትን ለሚረጋገጥ የተዘጋጀ መመሪያ ቁጥር 802/2013

የአገሪቱ የሎጂስቲክስ ዘርፍ አፈጻጸም ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ የሙልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎትን ለግል ባለሃብት ክፍት እንዲሆን በማድረግ ጠንካራና ተወዳዳሪ አገልግሎት ሰጪ እንዲፈጠር ማድረግ እንዲሁም ዘርፉ በወድድር እንዲመራ ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በማኘቱ፤

የአገሪቱ ዓለም አቀፍ የገቢ እና የወጪ ንግድ ዕቃ ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ በዓይነትም ሆነ በማጠን እያደገ መጥቷል፡፡ በመሆኑም የአገሪቱ የዓለም አቀፍ ንግድ ዕቃ በአንድ የሙልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ አገልግሎቱን በበቂ ሁኔታ ተደራሽ ማድረግ እንደማይቻል በመታመኑ፤

በመንግስት የልማት ድርጅት የተያዘውን የሙልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት ለግል ባለሃብቱ ክፍት በማድረግ አገልግሎቱ በወድድር እንዲመሰረት በማስቻል የተገልጋዩንና የህዝብን ተጠቃሚነት ብሎም የአገልግሎት ጥራትንና ተደራሽነትን ሚረጋገጥ በማስፈለጉ፤

የሙልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎችን ቁጥር ማሳደግ አገሪቱ በዓለም አቀፍ የገቢ እና ወጪ ንግድ ለትራንስፖርት፣ ለባሕር ወደብ ቆይታ፣ ለመጋዘን ቆይታ በውጭ ምንዛሪ የምታወጣውን ወጪ በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው በመታመኑ፤

## Multimodal Transport Operators Commercial Licensing and Competency Certification Directive no. 802/2021

**Whereas**, the necessity to enhancing the performance of the logistics sector, creating efficient and strong service providers and realising competition led sector requires opening up of the multimodal transport system;

**Whereas,** the country's import and export trade increased significantly from time to time by type and volume and consequently it is believed that realization of effective multimodal transport service by the sole operator is not possible;

**Whereas**, the necessity of opening multimodal transport service that has been restricted to public enterprise to private investors to ensure that customers and the public at large are benefited from the quality of service, competition, and accessibility to it;

**Whereas,** increasing the number of multimodal transport service providers is believed to have a significant contribution in reducing the country's foreign currency expenditure related to international import and export trade transport cost, dwell time, and storage at seaport;

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2009 አንቀጽ 21 (4) (በ) እና በሜሪታይም ዘርፍ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 549/1999 አንቀጽ 18 (ለ) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት አከናዋኝ የንግድ ስራ ፍቃድ ለማስጠት እና ብቃት የሚረጋገጥበትን ሁኔታ ለመወሰን ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የብቃት ማረጋገጫ እና ንግድ ሥራ ፈቃድ መመሪያ ቁጥር 802/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አዋጁ የተሰጡ የቃላት ትርጉሞች እንደተጠበቁ ሆነው የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "**አዋጅ**" ማለት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 548/1999 ነው፣
2. "**ባለሥልጣን**" ማለት የሜሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ነው፣
3. "**አከናዋኝ**" ማለት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ማለት ነው፣
4. "**ድርጅት**" ማለት የመንግስት የልማት ድርጅት ነው፣
5. "**ኩባንያ**" ማለት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት የተቋቋመ አክሲዮን ማህበር ወይም ኃለፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበር ነው፣
6. "**በቅንጅት የሚደረግ ኢንቨስትመንት**" ማለት የአገር ወስጥ ባለሃብት እና የውጭ ባለሃብት ወይም እንደውጭ ባለሃብት መቆጠር የፈለገ ሚደበኛ ነዋሪነቱ በውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊ ጋር በቅንጅት የሚደረግ ኢንቨስትመንት ነው፣

**NOW THEREFORE**, in accordance with the commercial registration and licensing proclamation no.980/2016 Article 21 (4) (j) and exercising the power bestowed upon it by proclamation no.549/2007 Article 18 (b) of maritime sector administration, the ministry of transport issued this directive to determine issuance of multimodal transport operators commercial licensing and certification of competency.

## PART ONE

## GENERAL Provisions

### 1. Short Title

This directive may be cited as "Multimodal Transport Operators Commercial Licensing and Competency Certification Directive no. 802/2021"

### 2. Definition

Notwithstanding the definitions given in the multimodal transport proclamation, unless the context requires otherwise, in this directive:

1. **Proclamation**" means Multimodal Transport of Goods Proclamation no.548/2007.
2. "**Authority**" means Maritime Affairs Authority.
3. "**Operator**" means Multimodal Transport Operator.
4. "**Enterprise**" means public enterprise.
5. "**Company**'' means share company or private limited company established in accordance with Ethiopian law.
6. "**Joint investment**" means an investment undertaken jointly by an Ethiopian investor and foreign investor or an Ethiopian permanently residing abroad and preferring treatment as a foreign investor.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

7. **"የንግድ የሥራ ፈቃድ"** ማለት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት በዚህ መመሪያ መሰረት በባለሥልጣኑ የተሠጠ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ነው፣

8. **"የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት"** ማለት በዚህ መመሪያ በተወሰነው ዝርዝር መስፈርት መሰረት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት የንግድ ሥራ ለመሰማራት የሚያስችል ብቃት መኖሩ ሰረጋገጥ ይህንኑ ስራ ለማከራት በባለሥልጣኑ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፣

9. **"ሚኒስቴር"** ወይም **"ሚኒስትር"** ማለት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፣

10. **"አንድ ወጥ የሆነ ታሪፍ"** ማለት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ከዕቃ መነሻ ወይም ዕቃወን ከተረከበበት ቦታ እስከ ማስረከቢያ ቦታ ድረስ ያለወን የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ወጪ ለደንበኛው የሚያሳወቅበት የተጠቃለለ የአገልግሎት ዋጋ ነው፣

11. **"ወኪል"** ማለት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ወክልና የተሰጠው ከኢትዮጵያ ወጪ ያለ በመያው የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን በተወከለበት ሀገር የተመዘገበና የስራ ፍቃድ ያለው ነው፣

12. **"ማስረከቢያ ቦታ"** ማለት በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ለሚጓጓዙ ገቢ ጭነቶች መዳረሻ እንዲሆን ባለስልጣኑ የተወሰነ ቦታ ማለት ነው፣

13. **"ቻርተሪንግ"** ማለት በባሕር ትራንስፖርት ዘርፍ አንድ የመርከብ ባለቤት መርከቡን የሚከራይበት ስርዓት ሆኖ የአገልግሎት አይነቱ በዋናነት በመደበኛ ፕሮግራም የማይሸፈን ነው፡፡

7. "**Business License**" means a valid business license issued by the authority for providing multimodal transport service.

8. "**Certificate of Competency**" means a certificate issued by the authority after having ensured it is competent to carry out multimodal transport service based on the criteria instituted under this directive.

9. "**Ministry**" or "**Minister**" means ministry or minister of transport.

10. "**Single rate**" means single logistics rate or tariff that the multimodal transport operator charges its customer for all the logistics and transport services rendered from origin to the place of final delivery of the goods.

11. "**Agent**" means a company registered and licensed in a foreign country and appointed by the multimodal transport operator to represent and act on behalf of it in a country it is registered.

12. "**Delivery place**" means place of destination for import goods transported by multimodal transport operator as designated by the authority.

13. "**Chartering**" is a non-scheduled service within the shipping industry where a shipowner hires out his/her vessel to a charterer.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማንኛውም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ እና የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሠነድ በተሠጠባቸው ማናቸውም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ውሎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለሚያስፈልጉ

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት ከባለሥልጣኑ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያገኝ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት ሥራን መሥራት ወይም መጀመር ወይም መቀጠል አይችልም፡፡

2. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት ከባለሥልጣኑ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያገኝ "የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ" የሚል ኃረግ የተጨመረበትን የንግድ ስም ማጠቀም አይችልም፡፡

3. በዚህ መመሪያ የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የንግድ ስራ ፍቃድ ሁለት አይነት ይሆናል፡ -

   ሀ. ከፎብ የግዢ ስርዓት መመሪያ ወጭ ለሆኑ ጭነቶች የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ

   ለ. በፎብ የግዢ ስርዓት መመሪያ ለሚጓጓዙ ጭነቶች የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ

## 3. Scope of Application

This directive shall be applicable on any multimodal transport operator and any multimodal transport contracts to which multimodal transport documents are issued.

## 4. Need for Business License

1. Any person shall not begin or perform or continue multimodal transport operator service without a business license from the authority.

2. Any person shall not use a trading name entitled "Multimodal Transport Operator" without obtaining a business license from the authority

3. This directive covers issuance of two types of business licenses and certificates of competency:

   A. Multimodal transport operators for transporting goods not covered by the FOB directive.

   B. Multimodal transport operators for transporting goods covered by the FOB directive

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

## ክፍል ሁለት

## ከፎብ የግዢ ስርዓት መመሪያ ውጭ ለሆኑ ጭነቶች የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የብቃት ማረጋገጫ የንግድ ስራ ፍቃድ

### ምዕራፍ አንድ፡ የብቃት ማረጋገጫ የንግድ ስራ ፍቃድ

#### 5. መሰረታዊ ብቁነት

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ አክሲዮን ማህበር፣ ኃለፊነቱ የተወሰነ የግል ማኀበር፣ በኢትዮጵያወያን ባለሃብቶች ወይም በኢትዮጵያወያንና በውጭ ባለሃብቶች በቅንጅት ኢንቨስትመንት የተቋቋመ ድርጅት ወይም በኢትዮጵያ ወስጥ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት የንግድ ሥራ መስክ ለመሠማራት በሕግ መብት የተሰጠው የመንግስት የልማት ድርጅት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የሥራ ፈቃድ ለማግኘት ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡

#### 6. የንግድ ሥራ ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል መስፈርት

1. የሚቋቋመው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ዋና መሥሪያ ቤት በኢትዮጵያ ወስጥ የሚገኝ መሆኑ፤
2. የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው የመልቲሞዳል ትራንስፓርት አከናዋኝነት ሥራን በአግባቡ ለማካሄድ እና የንግድ እንቅስቃሴወን ለመምራት የሚችል መሆኑን ለሚረጋገጥ የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡ -

   ሀ. የኩባንያው ወይም የቅንጅት ኢንቨስትመንት መመስረቻ ፅሁፍ፣ የመተዳዳሪያ ደንብ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማቅረብ፤

## PART TWO

## Certificate of Competency and Business License of Multimodal Transport Operators for goods not covered under the FOB Directive

### Chapter One:

### Certificate of Competency and Business License

#### 5. Basic Competency

Provided the criteria detailed in Article 6 of this directive are met, share company, private limited company, an enterprise established by Ethiopian investors or jointly with foreign investors based on Ethiopian law or a public enterprise legally empowered to get engaged in multimodal transport operation can apply to the authority for a multimodal transport operator license.

#### 6. Criteria for Business License Issuance

1. The head office of the multimodal transport operator shall be located in Ethiopia
2. A person submitting business license application for multimodal transport operator shall fulfill the following criteria to prove that it can properly conduct and manage its activities and business.

   A. Submit the company or joint venture establishment document, administrative manual and investment license.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

ለ. ኩባንያው ወይም ድርጅቱ በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ቢያንስ ብር 25 ሚሊዮን (ሃያ አምስት ሚሊዮን ብር) ካፒታል ያለው ሆኖ ከዚህ ወስጥ 10 ሚሊዩን በጥሬ ገንዘብ በታወቀ ባንክ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡ ከተቀማጭ ካፒታል ወስጥ 50% በዝግ የባንክ ሂሳብ የሚቀመጥ ሲሆን ቀሪው 15 ሚሊዮን ደግሞ በተለያዩ ንብረቶች ማለትም የመስክ መኪና (2)፤ የቢሮ መኪና (2)፣ የቢሮ ህንጻ እና የቢሮ ማልገያ ቁሳቁሶች ያለው መሆኑ በባለሙያ ግምት የሚረጋገጥ መሆኑ፤

ሐ. በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ውል መሠረት የሚጓጓዘው ዕቃ ቢጠፉ ወይም ቢጎዳ ወይም ቢዘገይ ወይም ከውል የሚነጩ ሌሎች የኃላፊነት ሁኔታዎች ቢኖሩበት አስፈላጊውን ካሣ ለመክፈል የሚያበቃ የመድን ዋስትና ከመድን ሰጪ ኩባንያ በራሱ ወይም በሌላ ውል በቀጠራቸው ድርጅቶች በኩል ያለው መሆኑ፤

መ. ገቢ ዕቃ ከባህር ወደብ እስከ ጭነቱ የሚጨረሻ መድረሻ ቦታ በማጓጓዝ ላይ እያለ በመጥፋቱ ወይም በመሠረቁ ምክንያት ለሚጠየቅ የመንግስት ቀረጥና ታክስ መሸፈኛ የሚውል የጉምሩክ ኮሚሽን በሚወስነው የአከፋፈል ዓይነትና የገንዘብ ማጠን ልክ የቀረጥና ታክስ ዋስትና ለማቅረብ የተሠጠ መተማመኛ መኖሩ፤

ሠ. ኩባንያው ወይም አንድና ከዚያ በላይ የሆኑት ባለድርሻዎቹ እንደ ድርጅት በጭነት ማስተላለፍ፣ በመርከብ ወኪልና፣ በባህር ማጓጓዝ፣ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ኦፕሬተርነት፣ በአየር ትራንስፖርት፣ በድንበር ተሻጋሪ የጭነት ትራንስፖርት፣ በወደብ ማስተዳደር ወይም ከነዚህ በአንዱ የሥራ መስክ ቢያንስ የ5 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው መሆኑ፤

3.በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ የሚከተሉትን የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ማሟላቱን ባለሥልጣኑ ማረጋገጥ አለበት፡ -

B. The company/enterprise shall have paid-up capital of 25 million ETB (twenty-five million) in cash and assets, where-in at least 10 million shall be deposited in cash in a recognized bank and the remaining 15 million shall be in the form of different assets such as field vehicle (2), office vehicle (2), and office building and equipment that will be valued by a professional. 50% of the 10 million cash shall be deposited in block account.

C. Shall have insurance cover from insurance company either on its name or through its contracting companies, to settle claims for damage, loss, delay, and other liabilities that might arise out of contractual obligations connected to the multimodal transport contract.

D. Provide customs bond according to customs commission requirement and payment modality to cover government tax and duties if the import goods are lost and stolen while they are in transit from the seaport to the final destination.

E. The company or one or more of the shareholders shall have at least five years of experience as a company or enterprise in one of the following fields: freight forwarding, ship agency, maritime transport, multimodal transport operator, air transport, cross-border freight transport, and port administration.

3. Notwithstanding the commercial registration and licensing proclamation no. 980/2016 and provisions of Article 5 of this directive, the authority shall verify fulfillment of the following competency criteria:

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

ሀ. ለሚያከናወነው ሥራ በሥራው ማጠንና በሠራተኞቹ ልክ የሚያስፈልጉ የቢሮ ማልገያ ቁሳቁሶች መኖሩ፣

ለ. የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥራን ለመምራት የሚያስችል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸው ወይም ቢያንስ በመጀመሪያ ዲግሪ ሠልጥነው በጭነት አስተላላፊነት፣ በትራንዚተርነት፣ በወደብ ኦፐረሽን፣ በድንበር ተሻጋሪ ትራንስፖርት ሥራአመራር ወይም ኦፕሬሽን፣ በመርከብ ወክልና፣ የሚታይም ህግ ወይም በሌሎች ዓለም አቀፍ የንግድ ሎጀስቲክስ አሠራሮች ቢያንስ የ6 ዓመታት የሥራ ልምድ ያላቸው ከ 8 ያላነሱ ሠራተኞች እና 2 ከፍተኛ የስራ አመራር ከላይ በተጠቀሱት ዘርፎች ቢያንስ የ 3 ዓመት ልምድ ያላቸው፤

ሐ. እንደ ሚልቲሞዳል አከናዋኝ ሃላፊነት ወስዶ ለሚያጓጉዛቸው ዕቃዎች የባህርና የየብስ ኢንሹራንስ ሽፋን ማቅረብ ወይም በሚልቲሞዳል ሥርዓት ለማጓጓዝ ሃላፊነት የወሰደባቸውን ዕቃዎች በባህር ወይም በየብስ እንዲያጓጉዙ በውል የሚቀጥራቸው አጓጓዦች በዓለም ዓቀፍ የባህር ትራንስፖርት የዋስትና አሠጣጥ ስርዓት ወይም በሚሁላለፉባቸው ሃገሮች የየብስ ትራንስፖርት ህግ መሰረት ለሚያጓጉዙት ጭነት ዋስትና ያላቸው መሆኑ፤ ሆኖም ግን ሙሉ ሃላፊነቱን ሚልቲሞዳል አከናዋኙ ይወስዳል፤

መ. ከሃገር ወስጥም ሆነ ውጭ ወኪሎቹ ዕቃን በባህርና በየብስ ከሚያጓጉዙ ኩባንያዎች፣ ከዓለም ዓቀፍ የባህርና የሃገር ወስጥ ደረቅ ወደቦች እንዲሁም ሌሎች ተቆጣጣሪ እና የንግድ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በቀላሉ መረጃና ትዕዛዝ ለመለዋወጥ የሚያስችል ሥራውን የሚመጥን የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ያለው፤

ሰ. በሃገር ወስጥ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ያለው ወይም መክፈት የሚችል ስለመሆኑ ማረጋገጫ የሚያቀርብ፤

A. Availability of adequate office equipment for the number of people employed and activities carried out.

B. Shall have qualified employees to carry out multimodal transport job properly. The company or enterprise shall have at least 8 trained employees holding certificate of competency or minimum first degree with 6 years and above experience, in freight forwarding, customs clearing, port operation, cross-border transport operation or management, ship agency, maritime law, and other international trade logistics operations. In addition, it shall also have 2 top managers having 3 years' experience in managerial position in the areas detailed above.

C. The multimodal operator shall procure and avail insurance cover for the goods it transports by sea and land or shall ensure that the ocean carrier sub contracted do have P&I cover and the hauliers also do have road transport liability cover according to the rules of the transit state. In any case, the multimodal transport operator bears full liability.

D. Shall have information communication to enable it easily communicate information and instructions with local and foreign agents, sea and land freight transport companies, international seaports and local dry ports, and other major stakeholders in the sector.

E. Shall present a document confirming that it either has or is capable of opening foreign currency account in Ethiopia.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

ረ. በአዋጁ አንቀጽ 8 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 ንዑስ-አንቀጽ (2) መሰረት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሠነድ ማዘጋጀት፣ ማተምና መስጠት የሚችል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት፡ የንግድ ሥራ ፈቃድ፤ እድሳት፤ እገዳና ስረዛ

### 7. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት

1. ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ በባለሥልጣኑ ተዘጋጅቶ በአመልካቹ የተሞላ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማጠየቂያ ቅጽ፤ የአገልግሎት ክፍያ እና ባለሥልጣኑ ከሚጠይቃቸዉ ሌሎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 እና 6 የተመለከቱትን አባሪ ማስረጃዎች ተሟልተው ሲቀርቡለት በመጀመሪያ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት የብቃት ማረጋገጫ ቀጥሎ ቋሚ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሠጣል፤

2. የንግድ ሥራ ፈቃዱ የሚሰጠው የንግድ ሥራ ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ አመልካቹ ለባለሥልጣኑ ሲከፍል ይሆናል፡፡

3. በዚህ መመሪያ መሠረት በባለሥልጣኑ የተሰጠ የንግድ ሥራ ፈቃድ እና የመጨ ብቃት ማረጋገጫ የመልቲሞዳል ትራንስፓርት አከናዋኝነት ሥራን ለማካሄድ የሚያስችል የሚጨረሻ የብቃት ማረጋገጫ እና የንግድ ሥራ ፍቃድ ይሆናል፡፡

### 8. የንግድ ሥራ ፈቃድ እድሳት

1. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ቋሚ የንግድ ሥራ ፈቃዱን ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በየዓመቱ ለባለሥልጣኑ እያቀረበ ማሳደስ አለበት፣

F. Prepare, print and issue multimodal transport document in accordance with Article 8 of the proclamation and Sub-Article 2 of Article 12 of this directive.

## Chapter Two: Business license Issuance, Renewal, Suspension, and Cancellation

### 7. Issuance of Business License

1. The authority shall first issue multimodal transport operator certificate of competency and then the permanent business license when an application pursuant to Article 5 of this directive attached with completed business license application form, service charge payment receipt, and other required documents according to Article 5 and 6 of this directive are submitted by the applicant.

2. The authority shall issue business license to applicants after the fee for the certificate of competency and business license is paid by the applicant.

3. Business license and certificate of competency issued by the authority under this directive, shall be the final certificate of competency and license to carry-out multimodal transport service.

### 8. Renewal of business license

1. The multimodal transport operator shall present its permanent business license to the authority and get it renewed every year.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

2. የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማደስ ባለሥልጣኑ የሚያዘጋጀው የማደሻ ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን በማሟላት የፈቃዱ ጊዜ ከማጠናቀቁ በፊት ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ ማቅረብ አለበት፤

3. የንግድ ሥራ ፍቃዱን ለማደስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 እና 6 የተጠቀሱትን መስፈርቶች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፤

4. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የንግድ ሥራ ፈቃዱን ለማስደስ የማስደሻ ክፍያ ይከፍላል፤

5. በተጠቀሰው የማደሻ ወቅት የንግድ ሥራ ፈቃዱን ያላደሰ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ በአንድ ወር ውስጥ ለማስደስ ካመለከተ ብቻ በገንዘብ ቅጣት ያሳድሳል፡፡

## 9. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ

1. የአዋጁና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ተጥሰው ሲገኙ በባለሥልጣኑ ውሳኔ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

2. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ የሚችልበት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ እገዳው ወይም ሥረዛዉ ከመተግበሩ ከሶስት ወራት በፊት በባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፣

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ የንግድ ሥራ ፈቃድን ሊያግድ ይችላል፡-
   ሀ. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የተሰጠውን ፈቃድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (5) መሰረት ካላሳደሰ፤

2. For renewal of the business license, the multimodal transport operator ought to complete the renewal application form prepared by the authority and submit along with other relevant documents to the authority two months before the expiry of the license.

3. The multimodal transport operator shall fulfill all the requirements detailed under Articles 5 and 6 of this directive when applying for renewal of business license.

4. At the time of renewing a business license, the multimodal transport operator is obliged to pay renewal service charge.

5. Those who failed to renew their business license within the renewal period will be allowed to renew with a penalty if only they apply within a month after expiry of the renewal period.

## 9. Suspension or Cancellation of Business License

1. The authority may prohibit or cancel the business license when the multimodal transport operator acts against the provisions contained in the proclamation and this directive.

2. In circumstances where there is a possibility of suspension or cancellation, the authority must issue warning notice 3 months before the effective date of suspension or cancellation of business license.

3. Notwithstanding the provisions contained under Sub-Article (1) of this Article, the authority may suspend the business license under any one of the following conditions:
   A. If the multimodal transport operator fails to renew its license according to Sub-Articles (2) and (5) of Article 8 of this directive.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

ለ. በአመታዊ ወይም በድንገት በሚደረግ ፍተሻ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰውን ሳያሟላ ሲገኝ፤

ሐ. ሥራን ለማሥራት በዚህ መመሪያና አከናዋኙ በገባው ውል ማሰረት ብቁ ሆኖ ሣይገኝ የቀረ እንደሆነ፤

መ. ፈቃዱ የታገደበት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ከባለሥልጣኑ የሚሰጡትን አስተያየቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ወስጥ አሟልቶ ሲገኝና ባለሥልጣኑ የሚወስነውን ቅጣት ከፍሎ እገዳው ይነሳለታል፤

ሠ. ፈቃዱ የታገደበት አከናዋኝ ፍቃዱ ከታገደበት ቀን ጀምሮ የመልቲሞዳል አገልግሎት ለመስጠት አዲስ ውል ሳይገባ ቀድሞ ውል የያዘባቸውን ሥራዎች ብቻ ያከናውናል፡፡

4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀጽ 1 አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሊሠርዝ ይችላል፡-

ሀ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(ሀ) ማሰረት የታገደበትን የንግድ ስራ ፍቃድ በአንድ ወር ወስጥ ሳያሳድስ ከቆየ ፤

ለ. የንግድ ሥራ ፈቃዱ የተገኘው በማታለል ወይም በማጭበርበር ወይም የሀሰት ማስረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ ከሆነ፤

ሐ. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በማንኛውም ዓይነት የማጭበርበር ድርጊት ወይም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት ሥራን አስመልክቶ አዋጁንና ይህን መመሪያ የሚጻረር ጥፋት ወይም የወንጀል ድርጊት መሥራቱ ከተረጋገጠ፤

B. If the annual or sudden inspection proves that the multimodal transport operator failed to fulfill requirements detailed under Sub-Article (3) of Article 8.

C. If it becomes incompetent and fails to comply with this directive and any other agreement it has signed.

D. Suspension of the license shall be lifted if the multimodal transport operator corrects all the remarks given by the authority within the given period and pays penalty fee as decided by the authority.

E. In the event the license is suspended, the multimodal transport operator shall only complete any work it has started before the suspension and shall not enter into a new contract.

4. Notwithstanding provisions under Sub-Article (1) of this Article, the authority may cancel the business license under any one of the following conditions.

A. If the multimodal transport operator fails to renew its suspended license within a month in line with Sub-Article 3 (A), of this directive.

B. If the license is obtained by fraud or deception or misrepresentation of documents.

C. If the multimodal transport operator is confirmed to have committed any kind of deception or offences or criminal acts against the proclamation and this directive.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

መ. የመልቲሞዳል ትራንስፖርትን ሥራ ለማሥራት በአንቀጽ 5 እና 6 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች በማጓደሉ ምክንያት በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት በወቅቱ ማስተካከል ካልቻለ፣

ሠ.የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የንግድ ሥራ ፈቃዱ በታገደበት ወቅት ቀድሞ ወል ከገባባቸው ውጭ አገልግሎት ማስጠቱ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

ረ.በአንቀፅ 9 ንዑስ-አንቀጽ (3) መሰረት ለተላለፈበት እገዳ ምክንያት የሆኑ ጉድለቶችን ባለሥልጣኑ በሰጠው የጊዜ ገደብ ወስጥ አስተካክሎ እገዳውን ያላስነሳ መሆኑ ሲታወቅ፣

ሸ. የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሰረዘበት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ አስፈላጊ ሁኔታዎችን አሟልቶ ከሁለት ዓመት በኋላ እንደገና ሊያመለክትና እንዳስፈላጊነቱ ታይቶ ሊፈቀድለት ይችላል፣

## 10. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለመመለስ

የሥራ ፈቃዱ እንዲሰርዝ የተወሰነበት ወይም የሥራ ፈቃዱን ለመመለስ የፈለገ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ በባለሥልጣኑ ከሚዘጋጅ ቅጽ ጋር የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡ -

1. የንግድ ሥራ ፈቃድ ለመመለስ ከሶስት ወራት በፊት ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ቅድሚያ ማሳወቅ አለበት፤

2. የንግድ ስራ ፍቃዱን ለመመለስ ጥያቄ ያቀረበ ወይንም ፈቃዱ በባለስልጣኑ የተሰረዘ አከናዋኝ
   - ሀ. ወል የያዘባቸው ሥራዎችን በሁለት ወራት ወስጥ አጓጉዞ ማስረከብ፣
   - ለ. አዲስ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት የማከናወን ስራ አይጀምርም

D. If it fails to correct the notice and warning given following the shortfall of the requirements detailed in Articles 5 and 6.

E. During the period of suspension, if it is confirmed that the multimodal transport has entered into a new contract other than completing existing contracts.

F. If it fails to correct the shortfalls that have been the cause for the suspension as per Sub-Article (3) of Article 9 and get the suspension lifted within the period specified by the authority.

G. A multimodal transport operator whose business license is cancelled can reapply after two years after having corrected the reasons and shortfalls for cancellation and may get permitted depending on the situation.

## 10. Return of Business License

A multimodal transport operator who wishes to return his license or whose license is cancelled shall complete the form prepared by the authority and fulfil the following

1. A multimodal transport operator who wishes to return his/her business license shall notify the authority in writing three months in advance.

2. A multimodal transport operator who puts the authority on notice for return of its business license or whose license is cancelled by the authority:
   - A. Shall transport and deliver all the goods accepted for transportation within two months.
   - B. Shall not enter new contracts

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በእጁ ያለውን የደንበኞች ዕቃ አጓጉዞ ማስረከብ ያልቻለ፡ -

   ሀ. ደንበኛው ለሚጠው ሌላ የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ሥራውን ያስተላልፋል፤

   ለ. ከደንበኛው የወሰደውን አገልግሎት ያልሰጠበት ክፍያ ካላ ታስቦ ተመላሽ ያደርጋል፤

4. በመንግሥት የሚፈልግበት ማንኛውም የግብር እና ሌሎች ግዴታዎች ነፃ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፤

5. የወሰደውን የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት የንግድ ፍቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ መመለስ አለበት፡ ፡

## ምዕራፍ ሶስት፡

## የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ተግባራት፣ ግዴታዎችና ክልከላ

### 11. የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ተግባራት

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የሚያከናወናቸው ሥራዎች የሚከተሉት ናቸው፡ -

3. Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, if the multimodal transport cannot transport and deliver the goods under its custody within two months:

   A. It shall transfer the goods to another multimodal transport operator selected by the customer.

   B. Any payment collected from the customer to whom no service is given shall be returned.

4. Shall present a document certifying that it is free from any tax-related and other obligations.

5. It shall return the multimodal transport operator license and competency certificate.

## Chapter Three:

## Duties, Obligations, and Prohibited Activities of the Multimodal Transport Operator

### 11. Duties of the Multimodal Transport Operator

Notwithstanding the provisions of the proclamation, the functions of the multimodal transport operator are the following:

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

1. ከዕቃ አስመጪው ወይም ከላኪው ጋር በሚያደርገው የሞልቲሞዳል ትራንስፖርት ውል ላይ በተቀመጡት ሁኔታዎች መሠረት ቢያንስ ሁለት የተለያዩ የማጓጓዣ ዓይነቶችን በመጠቀም ዕቃን በውጭ ሀገራት ከሚገኝ መነሻ ቦታ ተረክቦ በማጓጓዝ ሀገር ውስጥ በሚገኝ ማስረከቢያ ቦታ ወይም ለዕቃ ተረካቢ ማስረከብ፤ ወይም ዕቃን በሀገር ውስጥ ከሚገኝ መነሻ ቦታ ተረክቦ በማጓጓዝ በውጭ ሀገር በሚገኝ ማስረከቢያ ቦታ ለዕቃ ተረካቢ ማስረከብ፤

2. ዕቃዎችን የማቀናጀት፣ ዕቃዎችን ለያይቶ የማስረከብ፣ የዕቃዎች ማከማቻ ወይም ማቆያ አገልግሎት፣ የዕቃ ማስተናገጃ መሣሪያ አገልግሎት፣ የተርሚናል እና የኮንቴይነር ማስተናገድ አገልግሎት ማስጠት፤

3. በአዋጁ መሠረት የሞልቲሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ማዘጋጀት፣ ለዕቃ ላኪው ማስጠት፤

4. በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለሚያጓጉዘው ዕቃ ወቅታዊና የተሟላ መረጃ ለባለዕቃው እና ለመዳረሻ ጣቢያው በማስጠት የጭነቱን ፍሰት መከታተል እና መቆጣጠር፤

5. በሀገር ውስጥ የጉምሩክ ስርዓት በሚፈጸምባቸው ቦታዎች ወይም በመንግስት የሞልቲሞዳል ትራንስፖርት መዳረሻ ሆነው በተሰየሙ ሚፍቸውም ቦታዎች ብቻ ዕቃዎችን ለደንበኛው ማስረከብ ወይም እንዲቆዩ ማድረግ፤

6. የተረከበውን ዕቃ ደህንነት በማጠበቅ ከመነሻ ቦታ ከዕቃ ላኪው ወይም ወኪሉ በተረከበበት ሁኔታ ለተረካቢው ማስረከብ፤

7. ገቢ ዕቃ ከባህር ወደብ እስከ ጭነቱ የመጨረሻ መድረሻ ቦታ በማጓጓዝ ላይ እያለ በመጥፋቱ ወይም በመሠረቁ ምክንያት ለሚጠየቅ የመንግስት ቀረጥና ታክስ መሸፈኛ የሚውል በጉምሩክ ኮሚሽን የሚጠየቅ የጉምሩክ ዋስትና ማቅረብ፣

8. ህጋዊ ዕውቅና ባለው የውጭ ኦዲተር ሊመረመር የሚችልና የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 847/2006 የተከተለ የሂሳብ መዝገብ መያዝ ናቸው፡፡

1. In accordance with the terms and conditions of the multimodal transport contract concluded with the consignee or shipper; utilize at least two modes of transport and deliver the goods received at a place of origin in a foreign country to an inland destination or deliver to the consignee; or transport the goods received at an inland place of origin to a final place of delivery in a foreign country or deliver it to the consignee.

2. Provide consolidation and deconsolidation of goods, warehousing, cargo handling equipment, terminal and container handling services.

3. Prepare and issue multimodal transport document in accordance with the proclamation.

4. Provide current and complete information using communication technologies to cargo owners, and destination places and monitor status of shipments.

5. Deliver goods to inland custom clearing places or any places designated by the government as a multimodal transport destination.

6. Deliver goods in apparent good order and condition as was received from the shipper or his/her agent.

7. Provide customs bond pursuant to customs commission requirement to cover government tax and duties in case the import good is lost or stolen while it was in transit from the seaport to the final destination.

8. Maintain accounting records that can be audited by legally recognized external auditor in accordance with the financial reporting proclamation 847/2014.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

## 12. የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ግዴታዎች

በአዋጁ ላይ የተመለከቱት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሚልቲሞዳል ትራንስፓርት አከናዋኙ ግዴታዎች የሚከተሉት ናቸው፡ -

1. ዕቃ በሚጓጉዝባቸው የወጪ አገር ቅርንጫፍ ጽህፍት ቤት ወይም ወኪል ሊኖረው ይገባል፤
2. የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 8 ላይ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን ያሟላ ሰነድ ማዘጋጀት
   ሀ. የሰነድ መለያ ቁጥር፣
   ለ. የዕቃ ላኪው ስም፣
   ሐ. በላኪው የተጠቀሰ ከሆነ የተረካቢው ስም፣
   መ. የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ስምና ሚደበኛ የንግድ ሥራ ማከናወኛ ቦታው
   ሠ. ሚልቲሞዳል የትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃውን የተረከበበት ቀንና ቦታ፣
   ረ. ዕቃውን የጫነው የመርከብ ወይም የአይሮፕላን ስምና የጉዞ ቁጥር፣
   ሰ. ዕቃውን አጓጉዞ የሚያስረክቢያ ቦታ፣
   ሸ. የዕቃው ውጫዊ ሁኔታ መግለጫ
   ቀ. የዕቃው አጠቃላይ ሁኔታ ይህ ማለት ዕቃውን ለመለየት አስፈላጊ የሆኑ ሚሬ ምልክቶች፤ ዕቃው አደገኛ ከሆነ አደገኛነቱን የሚገልጽ መለያ፤ የዕሽጎቹን ወይም የነጠላ ዕቃውን ቁጥርና የዕቃውን አጠቃላይ ክብደት ወይም በመጠን የተገለጸ ከሆነ ይህንኑ በዕቃ ላኪ የሚሰጡ ዝርዝሮችን የሚገልጽ መሆን አለበት፣
3. አደገኛ የሆኑ ጭነቶችን በሚጓጉዝበት ወቅት ከዕቃ ላኪው የአደገኛ ጭነት መግለጫ ሰነዶችን ሚከብና ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት በወቅቱ ማቅረብ ይኖርበታል፣

## 12. Obligations of the Multimodal Transport Operator

In addition to complying with all the obligations detailed in the proclamation, the obligations of the multimodal operator are the following:

1. Shall appoint an agent or open branch office in every country it intends to render multimodal transport service
2. The multimodal transport document shall contain the following in addition to the details stated under Article 8 of the proclamation.
   A. Unique identification of the document
   B. Name of the shipper
   C. Name of the consignee as declared by the shipper
   D. Name and head office of the multimodal transport operator
   E. Place and date of receipt of the goods by the multimodal operator
   F. Name of vessel and voyage number or flight number
   G. Place of final delivery
   H. External condition of the goods
   I. Cargo condition and description, marks and numbers, if the goods are dangerous, corresponding IMCO and UN number, gross and net weights as declared by the shipper
3. Shall collect dangerous goods declaration and other relevant documents from the shipper when accepting dangerous goods. These documents shall be sent to the concerned regulatory authorities timely.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

4. የተረከበውን ዕቃ በተመለከተ ባለቤቱ ስለ ዕቃው መረጃ ማወቅ በፈለገበት በማንኛውም ጊዜ ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴን በማጠቀም ለባለዕቃው በሚሰጥ ቁጥር አማካኝነት እንዲከታተል ማመቻቸት አለበት፤

5. ዕቃውን አጓጉዞ በሚልቲሞዳል ሰነዱ በተገለጸው የመጨረሻ መዳረሻ ቦታ ከመድረሱ በፊት አስቀድሞ በደብዳቤ ወይም በኢሜይል ወይም በፋክስ ወይም በስልክ ቴክስት ወይም በሌላ በማናቸውም ዓለም አቀፍ መገናኛ ዘዴ በአድራሻ ለባለዕቃው እና በግልባጭ ዕቃው ሚራገፊያ ቦታ ላይ ለሚገኝ የደረቅ ወደብ ወይም ተርሚናል ኦፕሬተር ማሳወቅ፤

ሀ. በጭነት መኪና ለሚጓጓዙ ዕቃዎች ከ48 ሰዓት በፊት

ለ. በባቡር ለሚጓጓዝ ዕቃዎች ከ12 ሰዓት በፊት

6. ለባለዕቃው የተላኩ መልዕክቶችን እንዲሁም ከደንበኞች ጋር የተደረጉ የፋይናንስ ልውውጦች፣ የሥራ ግንኙነቶችንና ከሥራው ጋር የተያያዙ የተሟሉ መረጃና ሰነዶችን ሚደራጀት ሪኮርዶችን መመዝገብ እና እስከ አምስት አመት ድረስ ይዞ ማቆየት፤

7. የደንበኞች መረጃ በተመለከተ ባለሥልጣኑ በደብዳቤ በሚጠይቅበት ወቅት አስፈላጊ ሰነዶችና መረጃዎችን ማቅረብ፤

8. የሀገሪቱን የውጭ ንግድ ህጎች እና የባለወደብ ሃገራት ህጎች እና አሰራሮችን ማወቅ እና መተግበር አለበት፤

9. ለማጓጓዝ በሃላፊነት የተረከበውን ዕቃ ደህንነት ማጠበቅ፤ ዕቃው በቁጥጥሩ ሥር እያለ ወይም በቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቱ ወይም በወኪሉ ወይም በሰራተኞቹ ጥፋት ወይም ስህተት ቢጠፉ፣ ቢበላሽ፣ ቢዘገይ፣ ቢጎዳ ኃላፊነቱን መውሰድ፤

4. Shall use modern ICT application and assign passwords to be used by cargo owners in the event they want to know the status of the goods under its custody at any time.

5. Shall notify the consignee with a copy to the concerned dry port or terminal operator by letter or fax or email or text or other acceptable means of communication:

   A. 48 hours before the arrival of the goods at the final place of delivery if the on carriage takes place by truck

   B. 12 hours before the arrival of the goods at the final place of delivery if the on carriage takes place by train

6. Shall compile and maintain records of all correspondences and financial transactions made with customers for up to five years.

7. Shall present information related to customers as and when required by the authority.

8. The operator shall comply with the rules of the country's foreign trade, and the rules and procedures of transit states.

9. Shall take care of the goods under its custody. It shall assume full responsibility for loss, damage and delay for the goods under its custody or under the custody of its agent or branch office.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

### 13. የተከለከሉ ተግባራት

ከባለሥልጣኑ የጽሁፍ ሚረጋገጫ ካላገኘ በስተቀር ማንኛውም የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የሚከተሉትን ሚፈጸም አይፈቀድለትም ፡-

ሀ. በሥራው ሂደት በሚያጋጥም የተረጋገጠ ኪሳራ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የካፒታል ማጠኑን መቀነስ፣

ለ. የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ሥራ እንዲያከናወንበት የተሰጠዉን የንግድ ስም መቀየር፡፡

## ምዕራፍ አራት፡

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 14. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

በዚህ መመሪያ ለባለሥልጣኑ የተሠጡ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ባለሥልጣኑ፡

1. የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት የንግድ ሥራ ፈቃድ የተሠጣቸዉን ወይም የሥራ ፈቃዳቸው የታገደዉን ወይም የተሠረዘዉን የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ዝርዝር የያዘ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ወቅታዊ ሚረጃ አዘጋጅቶ ያወጣል፤
2. የአዋጁና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ተጥሰው ሲገኙ እንደተጥፋቱ ክብደት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እና 9 መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤
3. የአዋጁንና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ዝርዝር የአሰራር ስርዓት አዘጋጅቶ ስራ ላይ ያወላል፡፡

### 13. **Prohibited Activities**

Unless authorized by the authority in writing, the multimodal transport operator is not allowed to perform or carry out any of the following:

A. Reduction in the capital required unless bankrupted

B. Changes to trademark and or name

## Chapter Four:

## Miscellaneous Provisions

### 14. **Powers and Duties of the Authority**

Notwithstanding the powers and duties entrusted to the authority by this directive, the authority:

1. Shall compile and prepare information related to issuance, suspension and cancellation of multimodal transport business license and shall make it public.
2. Takes appropriate administrative measure as per Articles 8 and 9 when the provisions of this directive and proclamation are violated by the multimodal transport operator.
3. Prepares detailed working procedure to make the implementation of the provisions of the proclamation and this directive possible.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

## 15. የጉምሩክ ኮሚሽን ስልጣንና ተግባር

1. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ጭነትን ከባሕር ወደብ ወደ ማስረከቢያ ቦታ በማጓጓዝ ላይ እያለ ዕቃ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ ከመንግስት ለሚጠየቅ ቀረጥና ታክስ መሸፈኛ የሚውል አስፈላጊውን የጉምሩክ ዋስትና በማሟላት ከባህር ወደብ ወደ ሀገር ውስጥ ማስረከቢያ ቦታ እንዲያጓጉዝ ያመቻቻል፣ ይከታተላል፤

2. በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚጓጓዙ ዕቃዎች መዳረሻ ቦታ በባለስልጣኑ ተሰይሞ በደብዳቤ ሲደርሰው ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በማቋቋም አገልግሎት ይሰጣል፤

3. በማናቸውም ሁኔታ አገልግሎት ከመስጠት የታገዱ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች ከባለስልጣኑ በደብዳቤ ሲደርሰው ከመልቲሞዳል አከናዋኝ ጋር የተያያዘ የጉምሩክ አገልግሎት እንዳያገኝ ያደርጋል፤

## 15. Power & Duties of the Customs Commission

1. The customs commission shall enable and monitor the multimodal transport operator to transport uncustomed goods from the seaport to the place of final destination under a customs bond to cover government tax and duties in the event the goods are lost or stolen while in transit.

2. Shall open branch office and render services at place of final delivery designated by the authority upon receipt of designation letter from the authority.

3. Shall prohibit rendering services to suspended operators upon receipt of letter from the authority.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

# ክፍል ሶስት፡

## በፎብ የግዢ ስርዓት መመሪያ ለሚጓጓዙ ጭነቶች የመልቲሞል ትራንስፖርት አከናዋኝ የብቃት ሚረጋገጫ የንግድ ስራ ፍቃድ

## ምዕራፍ አንድ፡

## የብቃት ሚረጋገጫ እና የንግድ ስራ ፍቃድ

### 16. መስረታዊ ብቁነት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተቋቋመ አክሲዮን ማህበር፣ ኃለፊነቱ የተወሰነ የግል ማንበር፣ በኢትዮጵያወያንና በውጭ ባለሃብቶች በቅንጅት ኢንቨስትመንት የተቋቋመ ድርጅት ወይም በኢትዮጵያ ወስጥ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት የንግድ ሥራ ማከ ለመሠማራት በሕግ መበት የተሰጠው የመንግስት የልማት ድርጅት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) ስር የተደነገገዉ ቢኖርም ሚኒስቴር መስራቤቱ ለወደፊት የአከናዋኞቹን አዎንታዊ ወጤት እያየ ቁጥራቸወን ሊጨምር የሚችልበት ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ ባላቸው አደረጃጀትና የካፒታል ማጠን በቀዳሚነት የሚመረጡ ከአምስት ያልበለጡ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች ይሆናሉ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2) መሠረት በመልቲሞዳል ትራስፖርት አከናዋኝነት የሚሰሙሩ ኩባንያዎችን በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 ላይ በተመለከቱት እና ባለሥልጣኑ ወደፊት በሚያወጣው የማወዳደሪያ መስፈርት መሠረት በሚከሄድ ግልፅ ወድድር የሚመረጡ ይሆናሉ፡፡

# PART THREE:

## Certificate of Competency and Business License of Multimodal Transport Operators for goods covered under the FOB Directive

## CHAPTER ONE:

## License and Certificate of Competency

### 16. Basic Competency

1. Provided the criteria detailed in Article 17 of this directive are met, a share company, private limited company, an enterprise established jointly by Ethiopia and foreign investors based on Ethiopian law, or a public enterprise legally empowered to get engaged in multimodal transport operation can apply to the authority for a multimodal transport operator license.

2. Despite the provisions stated under Sub-Article (1) of this Article, in the beginning depending on their capital and organization no more than five multimodal transport operators will be selected. However, considering their performance and achievements the ministry may increase the number of operators.

3. Companies intending to engage in multimodal transport operation subject to Sub-Article (2) of this Article will be selected in a transparent way based on the criteria set in Article 17 of this directive and other criteria as may be announced by the authority.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

## 17. የንግሥራ ፈቃድ ለማስጠት የሚያስችል መስፈርት

1. የሚቋቋመው የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ዋና መሥሪያ ቤት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፤

2. የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው የሚልቲሞዳል ትራንስፓርት አከናዋኝነት ሥራን በአግባቡ ለማካሄድ እና የንግድ እንቅስቃሴውን መምራት የሚችል መሆኑን ለሚረጋገጥ የሚከተሉት መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡ -

   ሀ. የኩባንያው ወይም የቅንጅት ኢንቨስትመንት መመስረቻ ፅሁፍ፣ የመተዳደሪያ ደንብ እና የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማቅረብ፤

   ለ. በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾሙ ሆኖ ቢያንስ 75 በመቶ የሚሆኑት የቦርድ አባላት የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ በጭነት ማስተላለፍ፣ በመርከብ ወኪልና፣ በሺፒንግ ኦፕሬሽን፣ በወደብ ኦፕሬሽን፣ በጭነት ትራንስፖርት፣ በባንክና ኢንሹራንስ፣ የሚሪታይም ህግ ወይም በትራንዚትና የጉምሩክ መብት ማስፈፀም ሥራዎች የትምህርት ዝግጅት ኖሯቸው ሥራ አመራርና ኦፕሬሽን እንዲሁም ጥናትና ምርምር ከ5 ዓመት ያላነሰ የሥራ ልምድ ያላቸው መሆኑ፤

   ሐ. ኩባንያው ወይም ድርጅቱ በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ቢያንስ ብር 350 ሚሊዮን (ሶስት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ብር) ካፒታል ያለው ሆኖ ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 10 በመቶው በጥሬ ገንዘብ በታወቀ ባንክ የተቀመጠ ቀሪው 90 በመቶ ደግሞ በተለያዩ ንብረቶች ማለትም በትራንስፖርት መሳሪያዎች፣ በዕቃ ማስተናገጃ መሳሪያዎች፣ በመጋዘኖች እና በቢሮ ህንጻዎች ያለው መሆኑ፤ በጥሬ ገንዘብ በታወቀ ባንክ ከተቀመጠ 10 በመቶ ውስጥ ቢያንስ 50 በመቶ በዝግ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ ይኖርበታል፤

## 17. Criteria for Business License Issuance

1. The head office of the multimodal transport operator shall be located in Ethiopia.

2. A person submitting business license application for multimodal transport operator shall fulfill the following criteria to prove that it can effectively conduct and manage its activities and business:

   A. Submit the company or joint venture establishment document, administrative manual, and investment license.

   B. At least 75 percent of the board of directors assigned shall hold first degree and above and minimum experience of five years in areas related to freight forwarding, ship agency, ship operation, port operation, freight transport, banking, insurance, maritime law, customs clearance and in research and development in the sector.

   C. The company or enterprise shall have paid-up capital of 350 million ETB (three hundred fifty million) in cash and other assets, where-in at least 10% shall be deposited in cash in a recognized bank, and the remaining 90 percent shall be in the form of different assets such as transport equipment, cargo handling equipment, warehouses, and office building. 50% of the 10% cash deposited in a recognized bank shall be deposited in block account.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

መ. በሜልቲሞዳል ትራንስፖርት ውል መሠረት የሚያጓጉዘው ዕቃ ቢጠፋ ወይም ቢጎዳ ወይም ቢዘገይ ወይም ከውል የሚነጩ ሌሎች የኃላፊነት ሁኔታዎች ቢኖሩበት አስፈላጊውን ካሣ ለመክፈል የሚያበቃ የመድን ዋስትና ከመድን ሰጪ ኩባንያ በራሱ ወይም በሌላ ወል በቀጠራቸው ድርጅቶች በኩል ያለው መሆኑ፤

ሠ. ገቢ ዕቃ ከባህር ወደብ እስከ ጭነቱ የሚጨረሻ መድረሻ ቦታ በማጓጓዝ ላይ እያለ በመጥፋቱ ወይም በመሠረቁ ምክንያት ለሚጠየቅ የመንግስት ቀረጥና ታክስ ማሸፈኛ የሚውል የጉምሩክ ኮሚሽን በሚወስነው የአከፋፈል ዓይነትና የገንዘብ ማጠን ልክ የቀረጥና ታክስ ዋስትና ለማቅረብ የተሠጠ መተማመኛ መኖሩ፤

ረ. ኩባንያው ወይም አንድና ከዚያ በላይ የሆኑት ባለድርሻዎቹ እንደ ድርጅት በጭነት ማስተላለፍ፣ በመርከብ ወኪልና፣ በባህር ማጓጓዝ፣ በሜልቲሞዳል ትራንስፖርት፣ በአየር ትራንስፖርት፣ በድንበር ተሻጋሪ የጭነት ትራንስፖርት፣ በወደብ ማስተዳደር ወይም ከነዚህ በአንዱ የሥራ ማስክ ቢያንስ የ5 ዓመት የሥራ ልምድ ያለው መሆኑ፣

3. በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አመልካቹ የሚከተሉትን የብቃት ሚረጋገጫ መስፈርቶች ማሟላቱን ባለሥልጣኑ ሚረጋገጥ አለበት፡ -

ሀ. ለሚያከናወነው ሥራ በሥራው ማጠንና በሠራተኞቹ ልክ የሚያስፈልጉ በቂ የቢሮ መገልገያ ቁሳቁስ መኖሩ፤

ለ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) ላይ የተመለከተውን መስፈርት በሚያሟሉ እንዲሁም ቁጥራቸው ከ3 ባላነስና ከ13 ባልበለጠ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚመራ መሆኑ፤

D. Shall have insurance cover from insurance company either on its name or through its contracting companies, to settle claims for damage, loss, delay and other liabilities that might arise out of contractual obligations connected to the multimodal transport contract.

E. Provide customs bond pursuant to customs commission requirement and payment modality to cover government tax and duties if the import goods are lost and stolen while it was in transit from seaport till goods arrive at final destination.

F. The company or one or more shareholders shall have at least five years of experience as a company/enterprise in one of the following fields: freight forwarding, ship agency, maritime transport, multimodal transport, air transport, cross-border freight transport, and port administration.

3. Notwithstanding the provisions contained in the commercial registration and licensing proclamation no. 980/2016 and provisions of Article 16 of this directive, the authority shall verify fulfillment of the following competency criteria:

A. Avail adequate office equipment for the number of people employed and to the activities carried out.

B. In accordance with the criteria set in Sub-Article 2 (B), Article 17 of this directive, appoint maximum 13, minimum 3 members of board of directors.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

ሐ. የተሟላ ድርጅታዊ መዋቅር እንዲሁም የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሥራን ለመምራት የሚያስችል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸው ወይም በመጀመሪያ ዲግሪ ሠልጥነው በጭነት አስተላላፊነት፣ በጉምሩክ አስተላላፊነት፣ በወደብ አስተዳደር፣ በድንበር ተሻጋሪ ትራንስፖርት ሥራአመራር ወይም ኦፐሬሽን፣ በመርከብ ወክልና፤ የሚታይም ህግ ወይም በሌሎች ዓለም አቀፍ የንግድ ሎጂስቲክስ አሠራሮች ቢያንስ የ8 ዓመታት የሥራ ልምድ ያላቸው ከ15 ያላነሱ የሠለጠኑ ሠራተኞች እና ከነዚህ መካከል ቢያንስ 5ቱ የኩባንያው ወይም የድርጅቱን ከፍተኛ የሥራ ሚ ጨምሮ ማነረታዊ የሆኑትን ከፍተኛ የኦፐሬሽን ሥራ የሚምሩ ብቁ የሥራ ሚዎች ያሉት መሆኑ፤

መ. በቦርዱ የፀደቀ ድርጅታዊ መዋቅር ያሉት ሆኖ የእንያዳንዱ የድርጅቱ ሠራተኛ የቅጥር ውል፣ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲሁም በቦርድ የጸደቀ የሥራ ሃላፊዎች የተሰየመበት ማስረጃ መኖሩ፤

ሠ. ባግባቡ የታጠረና ደህንነቱ የተጠበቀ በትንሹ 5 ሄክታር ቦታ በባለቤትነት ወይም ከ4 ዓመት ያላነስ ጊዜ ከራይ ያለው ሆኖ ከዚህ ወስጥ ቢያንስ 3 ሄክታር የለማ ተርሚናል እና ከ3,000 ካሬ ሜትር ያላነሰ ስፋት ያለው በኮንክሪትና በብሎኬት የተሰራ ዝግ መጋዘን ያለው መሆኑ፤

C. Shall have a proper organizational structure, and qualified employees to carry out multimodal transport job properly. The company/ enterprise shall have at least 15 trained employees holding first degree or certificate of competency with 8 years and above experience, in freight forwarding, customs clearing, port operation management, cross-border transport operation or management, ship agency, maritime law, and other international trade logistics operations. At least 5 of them including members of the top management shall be competent operation managers able to manage important operations.

D. The company shall have organizational structure approved by the board. It shall also maintain records related to employee contracts, competency, work experience, and assignment of managers by the board of directors.

E. Own or rent for minimum of 4 years properly fenced and secured minimum 5 hectares of land. Out of this, a minimum of 3 hectares shall be well-developed terminal and 3,000 square meter warehouse built with concrete and blocket.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

ረ. አንድ ሪችስታከር ወይም ክሬን በባለቤትነት ወይም ቢያንስ በአራት ዓመት ኪራይ፣ በአንድ ጊዜ ቢያንስ 380 ኩንታል ማንሳት የሚችሉ 30 ድንበር ተሻጋሪ የጭነት ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነትና ሌሎች ተጨማሪ 40 ድንበር ተሻጋሪ የጭነት ተሽከርካሪዎችን በኪራይ፣ ቢያንስ አንድ ተርሚናል ትራክተር ከነተሳቢው እና ሁለት ፎርክሊፍት በባለቤትነት ማቅረብ የሚችል፤

ሰ. የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጥባቸው የውጭ ሀገራት ወደቦች ኩባንያው ወይም ድርጅቱ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ወይም ወኪል ያለው ስለመሆኑ የጽሁፍ ማረጋገጫ ከየሃገራቱ የሚመለከታቸው የመንግስት ባለስልጣን ማቅረብ የሚችል እና 3 የሃገር ወስጥ ቅርንጫፎች ያሉት መሆኑ፣

ሸ. የኢትዮጵያ ገቢ ዕቃ መዳረሻ በሆኑ የውጭ ሀገራት የባህር ወደቦች ሥራውን የሚያስተባብረለት ሰራተኛ ወይም ወኪል ያለው መሆኑን፤

ቀ. እንደሚልቲሞዳል አከናዋኝ ሃላፊነት ወስዶ ለሚያጓጉዛቸው ዕቃዎች የባህርና የየብስ ኢንሹራንስ ሽፋን ማቅረብ ወይም በሚልቲሞዳል ሥርዓት ለማጓጓዝ ሃላፊነት የወሰደባቸውን ዕቃዎች በባህር ወይም በየብስ እንዲያጓጉዙ በውል የሚቀጥራቸው አጓጓዦች በዓለም ዓቀፍ የባህር ትራንስፖርት የዋስትና አሠጣጥ ስርዓት ወይም በየሚተላለፉባቸው ሃገሮች የየብስ ትራንስፖርት ህግ መሰረት ለሚያጓጉዙት ጭነት ዋስትና ያላቸው መሆኑን ሚረጋገጥ የሚችል፤

F. Shall own or hire for not less than 4 years one reachstacker or crane, own 30 cross border trucks having minimum capacity of 380 quintals each, one tractor with trailer and two forklifts. It shall also hire and manage 40 more cross border trucks having minimum capacity of 380 quintals.

G. The company or enterprise shall present written certificate from the concerned government officials of the countries served by the operator, certifying that the operator has opened branch office or appointed an agent to oversee its operations. It shall also have 3 branch offices in Ethiopia.

H. Shall have a coordinating office or agent to oversee transit operations in discharging ports serving the country's import.

I. As a multimodal operator, the company shall procure and avail insurance cover for goods transported by sea and land under its responsibilities or the operator shall ensure that the ocean carriers and hauliers subcontracted to carry out sea and land transports do have P&I club cover and carrier's liability insurance for road transport as per the rules of the transit states.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

በ.ከሃገር ወስጥም ሆነ ውጭ ወኪሎቹ ዕቃን በባህርና በየብስ ከሚያጓጉዙ ከባንያዎች፣ደንበኞች፣ የሃገር ወስጥ ደረቅ ወደቦች፣ እንዲሁም ሌሎች ተቆጣጣሪ ባለድርሻ አካላት ጋር በቀላሉ መረጃና ትዕዛዝ ለመለዋወጥ የሚያስችል ሥራውን የሚምን የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ያለው፤

ተ. በሃገር ወስጥ ባንኮች የውጭ ምንዛሪ የሂሳብ ያለው ወይም መክፈት የሚችል ስለመሆኑ ሚረጋገጫ የሚያቀርብ፤

ቸ. በአዋጁ አንቀጽ 8 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 ንዑስ-አንቀጽ (6) መሰረት የተዘጋጀ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሠነድ ማዘጋጀት፣ማተምና ማሣተም የሚችል፤

## ምዕራፍ ሁለት፡ የንግድ ሥራ ፈቃድ፤ እድሳት፤ እገዳና ስረዛ

### 18. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለማሰጠት

1.ባለሥልጣኑ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ በባለሥልጣኑ ተዘጋጅቶ በአመልካቹ በሚገባ የተሞላ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማጠየቂያ ቅጽ፤ የአገልግሎት ክፍያ እና ባለሥልጣኑ ከሚጠይቃቸዉ ሌሎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 እና 17 የተመለከቱትን አባሪ ማሥረጃዎች ተሟልተው ሲቀርበለት በመጀመሪያ አመልካቹ ባቀረበው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝት የብቃት ሚረጋገጫ ቀጥሎ ቋሚ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሠጣል፡፡ ሆኖም ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው በአንቀጽ 16 ንዑስ-አንቀጽ (2) መሰረት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለሚመረጡ ድርጅቶች ብቻ ይሆናል፡፡

A. Shall have information communication technologies that will enable to easily communicate information and instructions with local and foreign agents, customers, sea and land freight transport companies, local dry ports, and other regulatory authorities including major stakeholders in the sector.

B. Shall present a document confirming that it either has or is capable of opening foreign currency account.

C. Prepare, print and issue multimodal transport document in accordance with Article 8 of the proclamation and Sub-Article 6 of Article 23 of this directive.

## Chapter Two: Business license Issuance, Renewal, Suspension and Cancellation

### 18. Issuance of Business License

1. The authority shall first issue multimodal transport operator certificate of competency and then the business license when an application pursuant to Article 16 of this directive attached with completed business license application form, service charge payment receipt and other required documents according to Article 16 and Article 17 of this directive is submitted by the applicant. However, this will be applicable to companies selected by the ministry in line with Sub-Article (2) of Article 16.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

2. በዚህ አንቀጽ፣ ንዑስ-አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም አመልካቹ በአንቀጽ 16 እና 17 ላይ የተመለከቱትን ሁሉንም ማስፈርቶች ባንድ ጊዜ ማሟላት ካልቻለ የተወሰኑትን ማስፈርቶች ብቻ እንዲያሟላና ጊዜያዊ ፈቃድ ተሰጥቶት አገልግሎት መስጠት እንዲጀምር ሊጠይቅና በባለስልጣኑ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡ ይሁንና አመልካቹ ጊዜያዊ ፈቃድ ሊሠጠው የሚችለው የሚከተሉትን ዝቅተኛ ማስፈርቶች አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነው፡፡ እነሱም፦ -

ሀ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 ላይ የተመለከቱትን ሁሉንም ማስፈርቶች፤

ለ. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17፤ ንዑስ-አንቀጽ (2) (ሀ፣ ለ፣ መ፣ ሠ እና ረ)፣ ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ፣ ለ፤ ሐ፤ መ፤ ሰ፤ ሸ፤ ቀ፤ በ፤ ተ እና ቸ)፤ እንዲሁም ንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተመለከቱትን ማስፈርቶች፤

ሐ. በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ቢያንስ ብር 228 ሚሊዮን (ሁለተ መቶ ሃያ ስምንት ሚሊዮን ብር) ካፒታል ያለው ሆኖ ከዚህ ውስጥ ቢያንስ 10 በመቶው በጥሬ ገንዘብ በታወቀ ባንክ የተቀመጠ ቀሪው 90 በመቶ ደግሞ በተለያዩ ንብረቶች ማለትም በትራንስፖርት መሳሪያዎች፣ በዕቃ ማስተናገጃ መሳሪያዎች፣ በመጋዘኖች እና በቢሮ ህንጻዎች በባለሙያ ግምት የሚሰላ፤ በጥሬ ገንዘብ በታወቀ ባንክ ከተቀመጠ 10 በመቶ ውስጥ ቢያንስ 50 በመቶ በዝግ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ ይኖርበታል፤

መ. ባግባቡ የታጠረና ደህንነቱ የተጠበቀ በትንሹ 3.5 ሄክታር ቦታ በባለቤትነት ወይም ከ4 ዓመት ያላነሰ ጊዜ ኪራይ ያለው ሆኖ ከዚህ ወስጥ ቢያንስ 2 ሄክታር የለማ ተርሚናል እና ከ2,000 ካሬ ሜትር ያላነሰ ስፋት ያለው በኮንክሪትና በብሎኬት የተሰራ ዝግ መጋዘን፤

2. Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, if the applicant is unable to fulfil all criteria stated under Articles 16 and 17 at once, it may fulfill some of the criteria and request the authority to provide a temporary license. However, a temporary license shall be issued to the applicant if only the following minimum criteria are met:

A. All criteria stipulated under Article 16 of this directive.

B. All criteria stipulated under Article 17, Sub-Article 2 (A, B, D, E, F), Sub-Article 3 (A, B, C, D, G, H, I, J, K, L), and Sub-Article 4 of this directive.

C. Paid-up capital of 228 million ETB (two hundred twenty-eight million) in cash and assets where-in 10 percent shall be saved in a recognized bank and the remaining 90 percent shall be in the form of different assets such as transport equipment, cargo handling equipment, warehouses, and office buildings valued as by professionals. 50% of the 10% cash deposited in a recognized bank shall be deposited in block account.

D. Own or rent for not less than 4 years properly fenced and secured land of minimum 3.5 hectares. Out of this, a minimum of 2 hectares shall be developed terminal and 2,000 square meter warehouse built with concrete and blocket.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

ሰ. አንድ ሪችስታከር ወይም ክሬን በባለቤትነት ወይም ቢያንስ በአራት ዓመት ኪራይ፣ በአንድ ጊዜ ቢያንስ 380 ኩ/ል ማጓሳት የሚችሉ 20 ድንበር ተሻጋሪ የጭነት ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነትና ሌሎች ተጨማሪ 30 ድንበር ተሻጋሪ የጭነት ተሽከርካሪዎችን በኪራይ እንዲሁም ቢያንስ አንድ ተርሜናል ትራክተር ከነተሳቢው እና አንድ ፎርክሊፍት በባለቤትነት የተመዘገበ ይሆናሉ፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (2) የተመለከተው ቢኖርም የጊዜያዊ ፈቃዱ የአገልግሎት ዘመን በማናቸውም ሁኔታ ከ1 ዓመት አይበልጥም፤

4. ጊዜያዊ ፈቃድ የተሰጠው የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ስለየሚሰጣቸው አገልግሎቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 25 ንዑስ-አንቀጽ (10) መሰረት ባለስልጣኑ በሚያወጣው የአሰራር ስርዓት ላይ ለይቶ ሊያቀርብ ይችላል ፤

5. የንግድ ሥራ ፈቃዱ የሚሰጠው የንግድ ሥራ ፈቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ ክፍያ አመልካቹ ለባለሥልጣኑ ሲከፍል ይሆናል፡፡

6. በዚህ መመሪያ መሠረት በባለሥልጣኑ የተሰጠ የንግድ ሥራ ፈቃድ እና የመጨ ብቃት ማረጋገጫ የሚልቲሞዳል ትራንስፓርት አከናዋኝነት ሥራን ለማካሄድ የሚያስችል የመጨረሻ የብቃት ማረጋገጫ እና የንግድ ሥራ ፍቃድ ይሆናል፡፡

E. Own or hire for not less than 4 years one reachstacker or crane, own 20 cross border trucks having a minimum capacity of 380 quintals each and additional 30 trucks on hire, own at least one tractor with trailer and one forklift.

3. Notwithstanding anything stated in Sub-Article (2) of this Article, temporary license period can not be extended beyond one year.

4. The services that will be rendered by multimodal transport operators holding a temporary license, may be determined by the authority and included in its administrative manual in accordance with Article 25 Sub-Article 10 of this directive.

5. The authority shall issue business license to applicants after the fee for the certificate of competency and business license is paid.

6. Business license and certificate of competency issued by the authority under this directive, shall be the final certificate of competency and license to carry-out multimodal transport service.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

## 19. የንግድ ሥራ ፈቃድ እድሳት

1. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ቋሚ የንግድ ሥራ ፈቃዱን ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በየዓመቱ ለባለሥልጣኑ እያቀረበ ማሳደስ አለበት፤

2. የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማደስ ባለሥልጣኑ የሚያዘጋጀው የማደሻ ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን በማሟላት የፈቃዱ ጊዜ ከማጠናቀቁ በፊት ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ ማቅረብ አለበት፤

3. የንግድ ሥራ ፍቃዱን ለማደስ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 16 እና 17 የተጠቀሱትን መስፈርቶች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፤

4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (1) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 18 ንዑስ-አንቀፅ (2) መሰረት የተሠጠ ጊዜያዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ አንድ አመት ሲሞላው በቋሚ ፈቃድ መተካት አለበት፤

5. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የንግድ ሥራ ፈቃዱን ለማሳደስ የማሳደሻ ክፍያ ይከፍላል፤

6. በተጠቀሰው የማደሻ ወቅት ቋሚ ወይም ጊዜያዊ የንግድ ሥራ ፈቃዱን ያላደሰ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ በአንድ ወር ውስጥ ለማሳደስ ካመለከተ ብቻ በገንዘብ ቅጣት ያሳድሳል፡፡

## 20. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለማገድ ወይም ስለመሠረዝ

1. የአዋጁና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ተጥሰው ሲገኙ በባለሥልጣኑ ውሳኔ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

## 19. Renewal of business license

1. The multimodal transport operator shall present its permanent business license to the authority and get it renewed every year.

2. For renewal of the business license the multimodal transport operator ought to complete the renewal application form prepared by the authority and submit along with other relevant documents to the authority two months before the expiry of the license.

3. The operator shall fulfill all the requirements detailed under Articles 16 and 17 of this directive when applying for renewal of business license.

4. Notwithstanding Sub-Article (1) of this Article, temporary license granted according to sub-Article (2) of Article 18 is valid only for one year and must be replaced by permanent business license.

5. At the time of renewing business license, the multimodal transport operator is obliged to pay renewal service charge.

6. Those who failed to renew their business license within the renewal period will be allowed to renew with penalty if only they apply within a month after expiry of the renewal period.

## 20. Suspension or Cancellation of Business License

1. The authority may prohibit or cancel the business license when the multimodal transport operator acts against the provisions contained in the proclamation and this directive.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

2.የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ የሚችልበት ሁኔታዎች ሲፈጠሩ እገዳው ወይም ስረዛዉ ከመተግበሩ ከሶስት ወራት በፊት በባለሥልጣኑ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

3.የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ የንግድ ሥራ ፈቃድን ሊያግድ ይችላል፡ -

ሀ. የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 ንዑስ--አንቀጽ (2) እና (6) ማሰረት ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ፈቃዱን ያላሳደሰ ከሆነ፤

ለ. የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ታሪፉን በተገቢው ጊዜ ለባለሥልጣኑ አሳወቆ ያላስመዘገበ ከሆነ፤

ሐ. በአመታዊ ወይም በድንገት በሚደረግ ፍተሻ የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሱትን ሳያሟላ ሲገኝ፤

መ. ሥራን ለመሥራት በዚህ መመርያና አከናዋኙ በገባው ዉል ማሰረት ብቁ ሆኖ ሣይገኝ የቀረ እንደሆነ፤

ሠ. ፈቃዱ የታገደበት አከናዋኝ ፍቃዱ ከታገደበት ቀን ጀምሮ የሜልቲሞዳል አገልግሎት ለማስጠት አዲስ ዉል ሳይገባ ቀደሞ ዉል የያዘባቸዉን ሥራዎች ብቻ ያከናዉናል፤

ረ. ፈቃዱ የታገደበት የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ከባለሥልጣኑ የሚሰጡትን አስተያየቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ወስጥ አሟልቶ ሲገኝና ባለሥልጣኑ የሚወስነዉን ቅጣት ከፍሎ እገዳው ይነሳለታል፣ ፍቃዱ ይታደሳል፤

2. In circumstances where there is a possibility of suspension or cancellation, the authority must issue warning notice 3 months before the effective date of suspention or cancellation of business license.

3. Notwithstanding provisions contained under Sub-Article (1) of this Article, the authority may suspend the business license under any one of the following conditions.

   A. If the multimodal transport operator fails to renew its permanent or temporary license according to Sub-Articles (2) and (6) of Article 19 of this directive.

   B. If the multimodal transport operator fails to file its tariff with the authority within the appropriate time.

   C. If the annual or sudden inspection proves that the multimodal transport operator failed to fulfill requirements detailed under Sub-Article (3) of Article 19.

   D. If it becomes incompetent and fails to comply with this directive and any other agreement it has signed.

   E. In the event the license is suspended, the multimodal transport operator shall only complete any work it has started before the suspension and shall not enter into a new contract.

   F. Suspension of the license will be lifted and renewal of the license will be granted if the multimodal transport operator corrects all the remark given by the authority with in the given period and pays penalty fee as decided by the authority.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

4. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሊሠርዝ ይችላል፡ -

ሀ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 3(ሀ) መሰረት የታገደበትን የንግድ ስራ ፍቃድ በአንድ ወር ወስጥ ሳያሳድስ ከቆየ፤

ለ. የሥራ ፈቃዱ የተገኘው በማታለል ወይም በማጭበርበር ወይም የሀሰት ማስረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ ከሆነ፤

ሐ. በማንኛውም ዓይነት የማጭበርበር ድርጊት ወይም የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት ሥራን አስመልክቶ አዋጁንና ይህን መመሪያ የሚጻረር ጥፋት ወይም የወንጀል ድርጊት መሥራቱ ሲረጋገጥ፤

መ. በአንቀጽ 16 እና 17 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች በማጓደሉ ምክንያት በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት በወቅቱ ማስተካከል ካልቻለ፤

ሠ. የንግድ ሥራ ፈቃዱ በታገደበት ወቅት ቀደሞ ወል ከገባባቸው ውጭ አገልግሎት ማስጠቱ ሲረጋገጥ፤

ረ. ባለሥልጣኑ ያወጣውን የሥራ አፈፃፀም ስታንዳርድ (በተለይም የዕቃዎች የባህር ወደብ ቆይታ ጊዜ፣ የአገልግሎት አሠጣጥ ጥራት ደረጃና የዕቃዎች አያያዝና ደህንነት አጠባበቅ) እንዲሁም የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የስነ-ምግባር ደንብ በተደጋጋሚ ማጓደሉ ሲረጋገጥ፤

4. Notwithstanding the provisions under Sub-Article (1) of this Article, the authority may cancel the multimodal transport operator business license under any one of the following conditions:

A. If it fails to renew suspended license within a month in line with Sub-Article 3 (A), of this Article.

B. If the license is obtained by fraud or deception or misrepresentation of documents.

C. If it is confirmed that the operator committed any kind of deception or offences or criminal acts against the proclamation and this directive.

D. If it fails to correct the notice and warning given following the shortfall of the requirements detailed in Articles 16 and 17.

E. During the period of suspension, if it is confirmed that it has entered into a new contract other than completing existing contracts.

F. If it repeatedly fails to comply with code of conduct and performance standard set by the authority in particular related to sea port dwell time of goods, quality of service, and safety to goods.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

## 21. የንግድ ሥራ ፈቃድ ስለመመለስ

የሥራ ፈቃዱ እንዲሰርዝ የተወሰነበት ወይም የሥራ ፈቃዱን ለመመለስ የፈለገ የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ በባለሥልጣኑ ከሚዘጋጅ ቅጽ ጋር የሚከተሉትን ማሟላት አለበት

1. የስራ ፈቃዱን ለመመለስ የፈለገ አከናዋኝ ከሶስት ወር አስቀድሞ ለባለስልጣኑ በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል

2. የንግድ ስራ ፍቃዱን ለመመለስ ጥያቄ ያቀረበ ወይንም የተሰረዘበት አከናዋኝ
   ሀ. ወል የያዘባቸው ሥራዎችን በሁለት ወራት ወስጥ አጓጉዞ ማስረከብ፣
   ለ. አዲስ የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት የማከናወን ስራ አይጀምርም

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ በሁለት ወር ጊዜ ወስጥ በእጁ ያለውን የደንበኞች ዕቃ አጓጉዞ ማስረከብ ያልቻለ፡-
   ሀ. ደንበኛው ለሚጠው ሌላ የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ሥራውን ያስተላልፋል፣
   ለ. ከደንበኛው የወሰደውን አገልግሎት ያልሰጠበት ክፍያ ካላ ታስቦ ተመላሽ ያደርጋል፤

4. በመንግሥት የሚፈልግበትን ማንኛውም የግብር እና ሌሎች ግዴታዎች ነፃ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ፤

5. የወሰደውን የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝነት የንግድ ፍቃድ እና የብቃት ማረጋገጫ መመለስ አለበት፡፡

## 21. Return of Business License

A multimodal transport operator who wishes to return his license or whose license is cancelled shall fulfill the following in addition to filling the form prepared by the authority.

1. A multimodal transport operator who wishes to return his/her business license shall notify the authority in writing three months in advance.

2. A multimodal transport operator who puts the authority on notice for return of its business license or whose license is cancelled;
   A. shall transport and deliver all the goods accepted for transportation within two months.
   B. Shall not enter into new contracts

3. Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, if the multimodal transport cannot transport and deliver the goods under its custody within two months;
   A. It shall transfer the goods to another multimodal transport operator selected by the customer.
   B. Any payment collected from the customer to whom no service is given shall be returned.

4. Shall present a document certifying that it is free from any tax-related and other obligations.

5. It shall return the multimodal transport operator license and competency certificate.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

## ምዕራፍ ሶስት፡

## የአከናዋኝ ተግባራት፤ ግዴታዎችና ክልከላ

### 22. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ተግባራት

በአዋጁ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የሚከናወናቸው ሥራዎች የሚከተሉት ናቸው፡:

1. ከዕቃ አስመጪው ወይም ከላኪው ጋር በሚያደርገው የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ውል ላይ በተቀመጡት ሁኔታዎች መሠረት ቢያንስ ሁለት የተለያዩ የማጓጓዣ ዓይነቶችን በመጠቀም ዕቃን በውጭ ሀገራት ከሚገኝ መነሻ ቦታ ተረክቦ በማጓጓዝ ሀገር ወስጥ በሚገኝ ማስረከቢያ ቦታ ለዕቃ ተረካቢ ማስረከብ፤ ወይም ዕቃን በሀገር ወስጥ ከሚገኝ መነሻ ቦታ ተረክቦ በማጓጓዝ በውጭ ሀገር በሚገኝ ማስረከቢያ ቦታ ለዕቃ ተረካቢ ማስረከብ፤
2. ዕቃዎችን የማቀናጀት፣ ዕቃዎችን ለያይቶ የማስረከብ፣ የዕቃዎች ማከማቻ ወይም ማቆያ አገልግሎት፣ የዕቃ ማስተናገጃ መሣሪያ አገልግሎት፣ የተርሚናል እና የኮንቴይነር ማስተናገድ አገልግሎት ማከናወን፤
3. በአዋጁ መሠረት የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ማዘጋጀት፣ ለዕቃ ላኪው ማስጠት፤
4. ባለሥልጣኑ በሚያጸድቀው አንድ ወጥ ታሪፍ የመልቲሞዳል ትራስፖርት አገልግሎት መስጠት፤
5. ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለሚያጓጉዘው ዕቃ ወቅታዊና የተሟላ መረጃ ለባለዕቃው፣ ለባለሥልጣኑ፣ ለመዳረሻ ጣቢያው ማስጠት እና የጭነቱን ፍሰት መከታተል እና መቆጣጠር፣
6. የተረከበውን ዕቃ ደህንነት በመጠበቅ ከመነሻ ቦታ ከዕቃ ላኪው ወይም ወኪሉ በተረከበበት ሁኔታ ለተረካቢው ማስረከብ፤

## Chapter Three:

## Duties, Obligations, and Prohibition

### 22. Duties of the Operator

Notwithstanding the provisions contained in the proclamation, the functions of the multimodal transport operator are the following:

1. In accordance with the terms and conditions stated in the multimodal transport contract concluded with the consignee or shipper; utilize at least two modes of transport and deliver goods received at a place of origin in a foreign country to an inland destination or deliver to the consignee or deliver goods received at an inland place of origin to a final place of delivery in a foreign country.
2. Provide consolidation and deconsolidation of goods, warehousing, cargo handling service, terminal and container handling services.
3. Prepare and issue multimodal transport document in accordance with the proclamation.
4. Provide multimodal transport service based on a single rate approved by the authority.
5. Provide current and complete information to cargo owners, authority, and destination places using modern information communication technology; monitor and control shipment flows.
6. Deliver goods in apparent good order and condition as was received from the shipper or his/her agent.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

7. በሀገር ወስጥ የጉምሩክ ስርዓት በሚፈጸምባቸው ቦታዎች ወይም በመንግስት የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት መዳረሻ ሆነው በተሰየሙ ሚፍቸወም ቦታዎች ብቻ ዕቃዎችን ለደንበኛው ማስረከብ ወይም እንዲቆዩ ማድረግ፤

8. ገቢ ዕቃ ከባህር ወደብ እስከ ጫኚ የሚጨረሻ መድረሻ ቦታ በማጓጓዝ ላይ እያለ በመጥፋቱ ወይም በመሠረቁ ምክንያት ለሚጠየቅ የመንግስት ቀረጥና ታክስ ማሽፈኛ የሚውል በጉምሩክ ኮሚሽን የሚጠየቅ የጉምሩክ ዋስትና ማቅረብ፤

9. ህጋዊ ዕወቅና ባለው የውጭ ኦዲተር ሊሚመር የሚችልና የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 847/2006 የተከተለ የሂሳብ ማዘገብ መያዝ ሥራ ላይ ማዋል፤

## 23. የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ግዴታዎች

በአዋጁ ላይ የተጠቀሱት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሚልቲሞዳል ትራንስፓርት አከናዋኝ ግዴታዎች የሚከተሉት ናቸው፡ -

1. ዕቃ በሚያጓጉዝባቸው የወጪ አገር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ወይም ወኪል ሊኖረው ይገባል፤

2. የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን ወይም ወኪሎችን ስምና አድራሻ የንግድ ሥራ ፈቃድ ካገኘ በኋላ ሥራ ከመጀመሩ 15 ቀናት አስቀድሞ በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ አቅርቦ ማስመዝገብ፤

3. የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ለሚሰጠው አገልግሎት ሥራ ላይ የሚያወለውን ታሪፍ፤ በቻርተሪንግ የሚወሰነውን ሳይጨምር ስራ ከመጀመሩ ወይም ከመቀጠሉ አንድ ወር አስቀድሞ ለባለስልጣን ማስሪያ ቤቱ ያቀርባል፤

7. Deliver goods at inland custom clearing places or any places designated by the government as multimodal transport destination.

8. Provide customs bond pursuant to customs commission requirement to cover government tax and duties in case the good intransit is lost or stolen.

9. Maintain accounting records in a form that can be audited by legally recognized external auditor in accordance with the financial reporting proclamation 847/2014.

## 23. Operator Obligations

In addition to complying with all the obligations detailed in the proclamation, the obligations of the multimodal operator are the followings:

1. Shall appoint an agent or open branch office in every country it intends to render multimodal transport service.

2. After securing its license and 15 days before commencement of service, the operator shall notify the names and addresses of its agents and branch offices in writing to the authority and get them registered.

3. The multimodal transport operator shall file its tariff, excluding rates fixed by chartering with the authority one month before commencement or continuation of its service.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

4. በባለሥልጣኑ የጸደቀ ታሪፍ በመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ቢያንስ ለ6 ወራት ሥራ ላይ ማቆየት ይኖርበታል፣ ሆኖም ግን አስገዳጅ ሁኔታዎች ከተፈጠሩ አከናዋኙ በማንኛውም ጊዜ ለባለሥልጣኑ ታሪፉ እንዲከለስ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፤

5. የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 3 የተጠቀሰው ቢኖርም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 25 ንዑስ-አንቀጽ (6) እና (7) ላይ እንደ ተገለጸው ባለሥልጣኑ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ታሪፉ ስለመጽደቁ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ምላሽ ያልሰጠ ከሆነ በመልቲሞዳል አከናዋኙ የተዘጋጀው ረቂቅ ታሪፍ በባለሥልጣኑ እንደጸደቀ ተቆጥሮ ሥራ ላይ ያውላል፤

6. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ሰነድ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 8 ላይ የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉትን መያዝ አለበት ፡-

ሀ. የሰነድ መለያ ቁጥር፣

ለ. የዕቃ ላኪው ስም፣

ሐ. በላኪው የተጠቀሰ ከሆነ የተረካቢው ስም፣

መ. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ስምና መደበኛ የንግድ ሥራ ማከናወኛ ቦታው፣

ሠ. መልቲሞዳል የትራንስፖርት አከናዋኙ ዕቃውን የተረከበበት ወይንም የጫነበት ቀንና ቦታ፣

ረ. ዕቃውን የጫነው የመርከብ ወይም የአይሮፕላን ስምና የጉዞ ቁጥር፣

ሰ. ዕቃውን አጓጉዞ የማስረከቢያ ቦታ፣

ሸ. የዕቃው ውጫዊ ሁኔታ መግለጫ

4. The tariff approved by the authority shall remain valid for at least 6 months. However, in the event the situation dictates change in the tariff, the operator can apply and request the authority for tariff revision.

5. In compliance with Sub-Article (3) of this Article and Sub-Articles (6) and (7) of Article 25, the authority has to approve the proposed tariff within one month time. The proposed tariff is considered approved if no replay is received within one month time.

6. The multimodal transport document shall contain the following in addition to the details stated under Article 8 of the proclamation.

   A. Unique identification of the document

   B. Name of the shipper

   C. Name of the consignee as declared by the shipper

   D. Name and head office of the multimodal transport operator

   E. Place and date of receipt or loading of the goods by the multimodal operator

   F. Name of vessel and voyage number or flight number

   G. Place of final delivery

   H. External condition of the goods

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

ቀ. የዕቃው አጠቃላይ ሁኔታ እና ዕቃውን ለማለየት አስፈላጊ የሆኑ ሜሪ ምልክቶች፣ ዕቃው አደገኛ ከሆነ አደገኛነቱን የሚገልጽ ማለያ፣ የዕሽጎቹን ወይም የነጠላ ዕቃውን ቁጥርና የዕቃውን አጠቃላይ ክብደት ወይም በማጠን የተገለጸ ከሆነ ይህንኑ በዕቃ ላኪ የሚሰጡ ዝርዝሮችን፤

7. አደገኛ የሆኑ ጭነቶችን በሚያጓጉዝበት ወቅት ከዕቃ ላኪው የአደገኛ ጭነት መግለጫ ሰነዶችን መረከብና ለሚመለከታቸው ተቆጣጣሪ አካላት በወቅቱ ማቅረብ፤

8. የተረከበውን ዕቃ በተመለከተ ባለቤቱ ስለ ዕቃው መረጃ ማወቅ በፈለገበት በማንኛውም ጊዜ ዕቃው ያለበትን ሁኔታ ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴን በመጠቀም ለባለዕቃው በሚሰጥ ቁጥር አማካኝነት እንዲከታተል ማመቻቸት፤

9. ዕቃውን አጓጉዞ በሚሊቲሞዳል ሰነዱ በተገለጸው የመጨረሻ መዳረሻ ቦታ ከመድረሱ አስቀድሞ በደብዳቤ ወይም በኢሜይል ወይም በፋክስ ወይም በስልክ ቴክስት ወይም በሌላ በሚፕቸውም ዓለም አቀፍ መገናኛ ዘዴ በአድራሻ ለባለዕቃው እና በግልባጭ ዕቃው ሚራገፊያ ቦታ ላይ ለሚገኝ የደረቅ ወደብ ወይም ተርሚናል ኦፕሬተር ማሳወቅ፡ -

ሀ. በጭነት መኪና ለሚጓጓዙ ዕቃዎች ከ48 ሰዓት በፊት

ለ. በባቡር ለሚጓጓዝ ዕቃዎች ከ12 ሰዓት በፊት

I. Cargo condition and description, Marks and numbers, If the goods are dangerous, corresponding IMCO and UN number, Gross and net weights as declared by the shipper

7. Shall collect dangerous goods declaration and other relevant documents from the shipper when transporting dangerous goods. These documents shall be sent to the concerned regulatory authorities timely.

8. Shall use modern ICT application and assign passwords to be used by cargo owners in the event they want to know the status of the goods under its custody at any time.

9. Shall notify the consignee with a copy to the concerned dry port or terminal operator by letter or fax or email or text or other acceptable means of communication;

   A. 48 hours before the arrival of the goods at the final place of delivery if the on carriage takes place by truck

   B. 12 hours before the arrival of the goods at the final place of delivery if the on carriage takes place by train

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

10. ለባለዕቃው የተላኩ ሜልዕክቶችና ከደንበኞች ጋር የተደረጉ የፋይናንስ ልወውጦች፣ የሥራ ግንኙነቶችንና ከሥራው ጋር የተያያዙ የተሟሉ ሚጃና ሰነዶችን ሜደራጀት ሪኮርዶችን መመዝገብ እና እስከ አምስት አመት ድረስ ይዞ ማቆየት፤

11. የደንበኞች ሚጃ በተማለከተ ባለሥልጣኑ በደብዳቤ በሚጠይቀበት ወቅት አስፈላጊ ሰነዶችና ሚጃዎችን ማቅረብ፤

12. የሀገሪቱን የወጭ ንግድ ህጎች እና የባለወደብ ሃገራት ህጎች እና አሰራሮችን ማወቅ እና መተግበር አለበት፤

13. ለማጓጓዝ በሃላፊነት የተረከበወን ዕቃ ደህንነት ማጠበቅ፤ ዕቃው በቁጥጥሩ ሥር እያለ ወይም በቅርንጫፍ ፅህፈት ቤቱ ወይም በወኪሉ ወይም በሰራተኞቹ ጥፋት ወይም ስህተት ቢጠፉ፣ ቢበላሽ፣ ቢዘገይ፣ ቢጎዳ ኃላፊነቱን መውሰድል፣

10. Shall compile and maintain records of all correspondences and financial transactions made with its customers for up to five years.

11. Shall present information related to customers as and when required by the authority.

12. The operator shall comply with the rules of the country's foreign trade, and rules and procedures of transit states.

13. Shall take care of the goods under its custody. It shall assume full responsibility for loss, damage and delay to for the goods under its custody or under the custody of its agent or branch office.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

## 24. የተከለከሉ ተግባራት

1. ከባለሥልጣኑ የጽሁፍ ሚረጋገጫ ካላገኘ በስተቀር ማንኛውም የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ የሚከተሉትን ሚፈጸም አይፈቀድለትም፡ –

ሀ. በሀገር ወስጥ ከሚገኝ ከሌላ የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ጋር መቀላቀል፣ ማንኛውም አይነት ሽርክና ሚፈጸም ወይም ሌላወን የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ተክቶ ይህንኑ ሥራ በባለቤትነት ማሥራት፣ ወይም በተሰሚራበት የሜልቲሞዳል ትራንስፓርት አከናዋኝነት ዘርፍ አካሄድ ላይ ጉልህ የሆነ ለወጥ ሚድረግ፤

ለ. በሥራው ሂደት በሚያጋጥም የተረጋገጠ ኪሳራ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር የካፒታል ማጠኑን መቀነስ፤

ሐ. የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ሥራ እንዲያከናወንበት የተሰጠወን የንግድ ስም መቀየር፤

2. ማንኛወም የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ አስቀደሞ ለባለሥልጣኑ ያስማዘገበው ታሪፍ ጸንቶ በሚቆይበት ጊዜ ወስጥ በታሪፉ ከተማለከተው በላይ ክፍያ ማጠየቅ፤

3. በአንድ የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ኩባንያ ወይም ድርጅት ወስጥ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሆነ ሰው በሌላ የሜልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ ኩባንያ ወይም ድርጅት በቦርድ አባልነት ማካተፍ አይችልም፡፡

## 24. Prohibited Activities

1. Unless authorized by the authority in writing, the multimodal transport operator is not allowed to perform or carry out any of the following:

A. Merger or joint venture of any kind with other domestic multimodal transport operator or operating on behalf of another multimodal transport operator or making noticeable and significant changes in the duties and responsibilities of multimodal transport.

B. Reduction in the capital required unless bankrupted

C. Changes to trademark or and name

2. Charging higher than the rate filed with the authority.

3. Becoming member of the board of directors of more than one multimodal transport operator.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

## ምዕራፍ አራት፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 25. የባለሥልጣኑ ሰልጣንና ተግባር

በዚህ መመሪያ ለባለሥልጣኑ የተሠጡ ሥልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ባለሥልጣኑ፡ -

1. የሥራ ፈቃድ የተሠጣቸዉን ወይም የሥራ ፈቃዳቸው የታገደባቸውን ወይም የተሠረዘባቸውን የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች ዝርዝር ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፤

2. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች በየጊዜው ሥራ ላይ የሚያወሉትን ታሪፍ በባለሥልጣኑ ማስመዝገባቸዉን ያረጋግጣል፤

3. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች የሚጠቀሙባቸዉ ሰነዶች ተስማሚ የአዘገጃጀት ሂደታቸዉም ቀላልና ቀልጣፋ እንዲሆን ከሚያዋስኑታቸዉ የባህር በር ካላቸው ጎረቤት አገሮች ጋር በመመካከርና በማዘጋጀት የሀገራችን ገቢ ንግድ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን ያደርጋል፤

4. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች የሚያቀርቡትና ባለስልጣኑ ያጸደቀውን ታሪፍ በሚስጥር ይይዛል፤

5. የመልቲሞዳል አገልግሎት ስታንዳርድን፣ የአሰራር ሥርዓት፣ የመልቲሞዳል አከናዋኝ ስነ-ምግባር ደንብን ያዘጋጃል፣ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፤

6. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 ንዑስ-አንቀጽ 3 መሠረት የቀረበውን ታሪፍ አግባብነት ከወቅቱ የዓለም አቀፍ ገቢያ ጋር ያነጻጽራል፤

## Chapter Four
## Miscellaneous Provisions

### 25. Powers and Duties of the Authority

Notwithstanding the powers and duties entrusted to the authority by this directive, the authority.

1. Shall compile and prepare information related to issuance, suspension and cancellation of multimodal transport business license and shall make it public.

2. Shall ensure that applicable tariffs of all multimodal transport operators are filed with the authority.

3. With a view to support and facilitate the country's import trade and in consultation with the coastal states, oversees the process and preparation of documents used by the multimodal transport operators are simple and easy.

4. Maintains the confidentiality of the tariff presented and approved by multimodal transport operators and the authority respectively.

5. Prepares service standards, working procedure and code of conduct of a multimodal transport operator, monitors and verifies its implementation.

6. Checks and compares the appropriateness of the tariff presented according to Sub-Article (3) of Article 23 against the international market.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

7.የጸደቀወን ታሪፍ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ለሚልቲሞዳል አከናዋኙ በጽሁፍ ያሳወቃል፣

8.በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 ንዑስ-አንቀጽ 2 (ሐ) መሠረት በሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ የሥራ ፈቃድ በተሰጠ ከ3 ወራት በኋላ ባሉት 5 የስራ ቀናት ወስጥ የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ በሚቀርብለት ጥያቄ ማስረት በዝግ የባንክ ሂሳብ የተቀማጠው ገንዘብ እንዲለቀቅ ለባንኩ በደብዳቤ ያሳወቃል፤

9.የአዋጁና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ተጥሰው ሲገኙ እንደጥፋቱ ክብደት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 20 ማስረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣

10. የአዋጁና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ዝርዝር የአሰራር ስርዓት አዘጋጅቶ ስራ ላይ ያውላል፡፡

## 26. የብሔራዊ ባንክ ስልጣንና ተግባር

1. የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች የሚያስፈልጋቸውን የውጭ ምንዛሬ በተማለከተ ባንኩ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር እና አፈጻጸሙን የሚከታተልበት ስርዓት ያዘጋጃል፤

2. በሚልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚጓጓዙ ዕቃዎች መዳረሻ ቦታ በባለስልጣኑ ተሰይሞ በደብዳቤ ሲደርሰው ለሁሉም የንግድ ባንኮች ያሳወቃል፤

3. በማኅቸወም ሁኔታ አገልግሎት ከማስጠት የታገዱ የሚልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች ከባለስልጣኑ በደብዳቤ ሲደርሰው ለሁሉም የንግድ ባንኮች ያሳወቃል፤

7. Informs the multimodal operator in writing approval of the tariff in less than one month time.

8. Advises the bank vide official letter to release the money deposited under blocked account according to Sub-Article 3(C) of Article 17 to the multimodal transport operator within 5 working days after expiry of 3 months from the date of issuance of the license.

9. Takes appropriate administrative measure as per Articles 20 when the provisions of this directive and proclamation are violated by the multimodal transport operator.

10. Prepares detailed working procedure to make the implementation of the provisions of the proclamation and this directive possible.

## 26. The Powers & Duties of the National Bank

1. In connection with the foreign currency required by the multimodal transport operators, the national bank of Ethiopia shall prepare foreign currency administration and monitoring manual.

2. Shall notify all commercial banks the destination places for goods transported under multimodal transport system upon receipt of designated letter from the authority.

3. Shall notify all commercial banks names of suspended multimodal transport operators upon receipt of letter from the authority.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

## 27. የጉምሩክ ኮሚሽን ስልጣንና ተግባር

4. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኙ ጭነትን ከባሕር ወደብ ወደ ማስረከቢያ ቦታ በማጓጓዝ ላይ እያለ ዕቃ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ ከመንግስት ለሚጠየቅ ቀረጥና ታክስ መሸፈኛ የሚውል አስፈላጊውን የጉምሩክ ዋስትና በማሟላት ከባህር ወደብ ወደ ሀገር ወስጥ ማስረከቢያ ቦታ እንዲያጓጉዝ ያመቻቻል፣ ይከታተላል፤

5. በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚጓጓዙ ዕቃዎች መዳረሻ ቦታ በባለስልጣኑ ተሰይሞ በደብዳቤ ሲደርሰው ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት በማቋቋም አገልግሎት ይሰጣል፤

6. በማናቸውም ሁኔታ አገልግሎት ከመስጠት የታገዱ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኞች ከባለስልጣኑ በደብዳቤ ሲደርሰው ከመልቲሞዳል አከናዋኝ ጋር የተያያዘ የጉምሩክ አገልግሎት እንዳያገኝ ያደርጋል፤

## ክፍል አራት፡

## የቅሬታ ማስተናገጃና የሌሎች ህጎች ተፈጻሚነት

## 28. በአስተዳደር ወሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ

1. የንግድ ሥራ ፍቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ማመልከቻ ወድቅ የተደረገበት አመልካች ወይም የንግድ ሥራ ፍቃድ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠው በኋላ ግዴታውን ባለመወጣቱ ምክንያት የተሰረዘበት ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ የተወሰደበት አመልካቹ ወይም አከናዋኝ በወሳኔው ቅር ከተሰኘ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 28 (2) መሠረት ለተቋቋመው ቅሬታ ሰሚ አካል ቅሬታውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፤

## 27. Power & Duties of the Customs Commission

1. The customs commission shall enable and monitor the multimodal transport operator to transport uncustomed goods from the seaport to the place of final destination under a customs bond to cover government tax and duties in the event the goods are lost or stolen while in transit.

2. Shall open branch office and render services at place of final delivery designated by the authority upon receipt of designation letter from the authority.

3. Shall prohibit rendering services to suspended operators upon receipt of letter from the authority.

## PART FOUR:

## Complaint Handling and Applicability of other Laws

## 28. Compliant Against Administrative Decision

1. A multimodal transport operator may lodge complaint in writing to the complaint handling body established according to Sub-Article (2) of Article 28 against administrative decisions related to non-acceptance of application for license or certificate of competency or cancellation of license or any administrative measure taken by the authority.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

2. ባለስልጣኑ በተሰጡ በአስተዳደራዊ ወሳኔዎች ላይ የሚቀርብን ቅሬታ መርምሮ ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም በዋና ዳይሬክተር ለሚወከል የሥራ ሃላፊ የወሳኔ ሃሣብ የሚያቀርብ የቅሬታ ሚስተናገጃ አካል ያቋቁማል፡፡ ይህንኑ ለተገልጋዮች ይፋ ያደረጋል፤

3. ማንኛወም ቅሬታ የቀረበበት ወሳኔ ቅሬታው ተመርምሮ ወሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ወሳኔው ተፈፃሚ አይሆንም፤ ሆኖም ግን የወሳኔው አለሚፈጸም በህዝብ ወይም በመንግሥት ላይ ሊመለስ የማይችል ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ በባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወሳኔ ተግባራዊ እንዲደረግ ሊወሰን ይችላል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሁኖ በባለስልጣኑ ወሳኔ ቅር የተሰኘ ቅሬታወን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ ይችላል፤

## 29. የሌሎች ሕጐች ተፈፃሚነትና የማሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ይህን መመሪያ የሚቃረን መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ወስጥ ለተሸፈኑት ጉዳዮች ተፈጻሚነት የለወም፤

2. በአሁኑ ጊዜ የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎትን እየተገበረ ያለ አከናዋኝ ይህ መመሪያ በወጣ በ3 ወር ጊዜ ወስጥ በፎብ የግዢ ስርዓት ለሚጓጓዙ ጭነቶች የመልቲሞል ትራንስፖርት አከናዋኝ ለመሆን የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ የንግድ ስራ ፍቃድ የሚሰጣቸው ይሆናል፤

2. The authority shall establish a complaint handling body that examines the complaint on administrative decision taken, and present its recommendation to the authority director-general or an officer duly authorized by the director-general. The establishment of complaint handling body shall be announced to the clients.

3. Enforcement of any decision against which a complaint is lodged shall stay until the complaint is processed and a final decision is made. However, the authority director general may order the enforcement of the decision where delay in enforcement may cause irreversible damage to the public interest.

4. Notwithstanding Sub-Article (3) of this directive, anyone disappointed by the authority's decision may lodge complaint to the ministry.

## 29. Applicability of other laws & Transitory Provisions

1. Any directive or traditional practice contradicting this directive shall not be enforceable with respect to issues covered under this directive.

2. An operator currently providing multimodal transport service shall apply for permanent license and certificate of competency for carriage of goods covered under FOB directive within 3 months commencing from the day this directive is announced.

https://t.me/HIMA_Xpress_Tax

3.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተጠቀሰው ማስረት ፍቃድ ካልወሰደ የሚጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በተጨማሪ 1 ወር ጊዜ ወስጥ ፍቃድ መውሰድ አለበት፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ወስጥ ቋሚ የሙያ ብቃት ሚረጋገጫ የሥራ ፈቃድ ካልወሰደ ሥራ መቀጠል አይችልም፡፡

3. An operator who fails to comply with Sub-Article (3) of this Article will be given a last warning with additional 1 month to apply and take its license. If license is not taken within the additional 1 month no operator shall be allowed to continue operation.

## 30. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በሚኒስቴሩ ተፈርሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## 30. Effective date

This directive shall come into force upon the publication by the ministry.

አዲስ አበባ

ሰኔ …. ቀን 2013 ዓ.ም

**ዳግማዊት ሞገስ**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የትራንስፖርት ሚኒስትር

Addis Ababa

June …., 2021

**DAGMAWIT MOGES**

MINISTER OF TRANSPORT,
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC
OF ETHIOPIA